# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ የቅድመ ልጅነት ዘመን እድገትና ትምህርት ፖሊሲ ማዕቀፍ

**2015 ዓ.ም**

# የትምህርት ሚኒስትር መልዕክት

በልጆች ዕድገት እና ትምህርት ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ልማት እና ማህበራዊ ፋይዳን ለማሳደግ ጉልህ ሚና ይጫወታል። ይህ የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ለልጆች ሁለንተናዊ እድገት የሚደረገውን ጥረት ያማከለና ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት። የልጅነት ዕድገትና እንክብካቤ ከጨቅላነት ጊዜ ጀምሮ አቀራረቡን ሁለንተናዊ በማድረግ በልጆች አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊና መንፈሳዊ ደህንነት እንዲሁም የመማር ዕውቀት ገጽታዎች ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት። ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ መንግስት፣ ሲቪል ማህበራት፣ ለጋሾች፣ ወላጆች እና ማህበረሰቦችን ጨምሮ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት በትብብር ሲሰሩ ነው። እንዲህ ዓይነት ጥረቶች ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፈውን የድህነት አዙሪት በማቋረጥ ሂደት ውስጥ መሠረታዊ አስተዋፅኦ ከማድረጋቸውም በላይ ለሀገር ብልጽግና መሠረት ይጥላሉ።

ሁለንተናዊ የሕፃናት ልማት በሚተገበርበት ወቅት ትምህርት በቅንጅት ስራና ግንዛቤን በመፍጠር ረገድ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት የተገነዘበው የኢፌዴሪ መንግሥት ለቅድመ ልጅነት ዘመን ዕድገትና ትምህርት ተገቢውን ትኩረት ይሰጣል። የሕፃናት ሁለንተናዊ ልማት በአገሪቱ አጠቃላይ የሰው ሀብት ልማት ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። ለዚህም መንግሥት ቀጣይነት ያለው ልማት እንዲኖር ለሰው ልጅ ካፒታል ልማት ቅድሚያ ለህፃናት በመስጠት ኢንቨስት እያደረገ ይገኛል። ስለሆነም በልጆች ላይ የሚሰሩ ሁሉም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች በተቀናጀ መልኩ በትብብር መስራት አለባቸው።

የኢትዮጵያ መንግስት ቃልከገባው አንዱ ለጤና መታወክ ተጋላጭ ለሆኑ፣ በዝቅተኛ የጥራት ደረጃ የሚገኘውን የቅድመ ትምህርት እና የማህበራዊ ችግሮችን በማቃለል ለሁሉም ሕፃናት ድጋፍና እድል በመስጠት የህፃናቱን ፍላጎት ማሟላት ነው። በሁለንተናዊ የህፃናት እድገት ውስጥ ከዋና ዋና ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ትምህርት ሚኒስቴር የተሻለ የትምህርት አካባቢ በመገንባትና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጥረቶችን በማስተባበርና ሁሉንም ተሳታፊ በማድረግ በዘርፉ የሚታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል።

ስለሆነም በዚህ በተሻሻለው የፖሊሲ ማዕቀፍ እያንዳንዱ ል ጅ ወደፊት አምራች ዜጋ እንዲሆን በሚደረገውሂደት የተቀናጀ ጥረትና ድጋፍ እንደሚጎለብት ይታሰባል። ትምህርት ሚኒስቴርም ሁሉም ባለድርሻ አካላት (ወላጆች፣ ማህበረሰቦች፣ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ የልማት አጋሮችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት) ቅድመ ትምህርትን ለማሻሻል የቅድመ-ልጅነት ዘመን ዕድገትና ትምህርት አገልግሎት በመስጠት ረገድ የሚጫወቱትን ሚና በግልፅ ይረዳል።

የዚህ ፖሊሲ ማዕቀፍ ትግበራ የቅድመ-ልጅነት ዘመን ዕድገትና ትምህርት አገልግሎቶች በተሻለ የገንዘብ ድጋፍ፣ አግባብነት፣ ጥራትና በውጤታማነት መመራቱና ማስተዳደር መቻሉ ተረጋግጦ ማየት ምኞቴ ነው። ስለዚህ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ለዚህ ፖሊሲ ማዕቀፍ ስኬትና ትግበራ የበኩላቸውን ተግባራት ሁሉ በላቀ መልኩ እንዲያሳኩ አሳስባለሁ።



**ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ**

የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር

# የጤና ሚኒስትር መልዕክት

የኢትዮጵያ መንግሥት የቅድመ ልጅነት ዘመን ትኩረት ማግኘት ያለበትና ብዙ ሥራ ሊሠራበት የሚገባ ወሳኝ የዕድገት ወቅት መሆኑን ይረዳል። በቅድመ ልጅነት ዘመን እድገት በተለይም በመጀመሪያዎቹ የሕፃናት ሶስት ዓመታት በመቀጠልም በመጀመሪያዎቹ ሰባት አመታት ዉስጥ የሚደረግ እንክብካቤና ጥበቃ ለሕፃናት ጤናማ እድገትና ለቀጣይ የህይወት ዘመናቸው መሰረት የሚጥልና እጅግ ወሳኝ ነው። በቅድመ ልጅነት ዘመን ለሕፃናት **ጥሩ የጤና አገልግሎት፣ በቂ እና የተመጣጠነ ምግብ፣ ደህንነትና ጥበቃ፣ ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ፣ ቀዳሚ ማነቃቃትና የቅድመ መደበኛ ትምህርት እድል** አለማቅረብ ሕፃናት በቀጣይ ህይወት ምርታማ ዜጋ እንዳይሆኑ ከማድረጉም በተጨማሪ የተሻለ ሕይወትን የመምራት ዕድላቸውን ያሰናክላል።

በቅድመ ልጅነት እድገትና መዳበር ወቅት በለጋ ሕፃናት ላይ የሚከሰት ጫና፣ ጉዳትና ጭንቀት አእምሮአቸዉ በአግባቡ እንዳይሠራ በማድረግ የመማር ችሎታቸዉን ያዳክማል። ይህም በአዋቂነት እድሜያቸው ሊደርሱበት ከሚችሉት ከፍተኛ የእድገት ደረጃ እንዳይደርሱ ሊገድባቸው ይችላል።

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የቅድመ ልጅነት እድገትና መዳበር ላይ መስራት ማለትም የህፃናቱን ጤና መጠበቅ እንዲሁም በአካል፣ በአእምሮ፣ በማህበራዊ ኑሮና በስሜት ክንዋኔያቸው በእድሜያቸው ሊደርሱበት በሚችሉት የላቀ የመዳበር ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ማገዝ ወደፊት ለሚኖራቸው ስኬታማ ህይወት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ከማድረጉ በተጨማሪ ለአገር መረጋጋት፣ ዘላቂ እድገት እና ልማት፣ ቀጥተኛ አስተዋፅኦ አለው። ቅድመ ልጅነት ላይ የታለሙ ፕሮግራሞችን መተግበር የሰው ሃይል ካፒታል ኢንቨስትመንትን የመመለስ ትልቅ አቅም አላቸው።


የቅድመ ልጅነት እድገት መዳበርና ትምህርት ፖሊሲ ማዕቀፍ ከጽንስ እስከ ሰባት ዓመት ዕድሜ ክልል ለሚገኙ ሕፃናትና ወላጆቻቸው ወይም ተንከባካቢዎቻቸው የሚሰጡ አገልግሎቶችን የሚያመላክት ሁሉን አቀፍ ፖሊሲና ፕሮግራምን ያካተተ ሲሆን የተለያዩ ሴክተሮችን ተሳትፎና ድጋፍ የሚፈልግ ነው።

ይህ የፖሊሲ ማዕቀፍ የምክክር ሂደት ውጤት ሲሆን፣ ሁሉን አቀፍ፣ ሊተገበር የሚችልና አዋጭ የሆነ የቅድመ ልጅነትን እንክብባኬና ትምህርት እንዲኖር መሠረት ይጥላል። የዚህ ፖሊሲ መተግበር የሀገራችን ሕፃናት የተሻለና ጤናማ የሕይወት ጅማሬ እንዲኖራቸው አንድ እርምጃ ወደፊት ለመራመድ የሚያስችል ሲሆን፣ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ኃላፊነት የሚሰማቸውና ምርታማ ዜጋ እንዲሆኑ የሚያግዝ አካባቢና ሁኔታን ይፈጥራል።

በቅድመ ልጅነት ዘመን ያለውን **የአመጋገብ፣ የጤና፣ ደህንነትና ጥበቃ, ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ, ቀዳሚ ማነቃቃትና የቅድመ መደበኛ ትምህርት** አገልግሎት ማዳረስና ማሻሻል ግልጽ የሆኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ያስገኛሉ። የዚህም ውጤታማነት የሚወሰነው በትምህርት፣ በጤና፣ በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሴክተር መስሪያቤቶች እና በሌሎችም ባለድርሻ አካላት መካከል በየደረጃው በሚኖረው ትብብር ነው።

ይህ የፖሊሲ ማዕቀፍ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በቅድመ ልጅነት ዘመን መሰጠት ያለባቸውን አገልግሎቶች በመስጠት ረገድ የሚኖራቸውን ሚና በግልጽ ያስቀምጣል። የወላጆችን፣ የማህበረሰቡን፣ የመንግሥት የልማት አጋሮችን እንዲሁም የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ኃላፊነት በዝርዝር ይገልፃል።

የእኛ ምኞትና ፍላጐት ፖሊሲውን በብቃትና በጥራት ተተግብሮ ለሁሉም ሕፃናት ተደራሽነት ያለው ፍትሐዊ የቅድመ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት አስተዳደር በሀገሪቱ እንዲሰርጽ ማድረግ ነው። ይህም የለጋ ሕፃናት እንክብካቤና ትምህርት በሀገራችን የልማት አጀንዳ ውስጥ ቅድሚያ እንዲያገኝ ይረዳል።



**ሊያ ታደሰ (ዶ/ር)**

የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር

# የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር መልዕክት

የቅድመ ልጅነት ዘመን በሰው ልጆች የእድገት ደረጃዎች ውስጥ ፈጣን አካላዊ፣ አዕምሮአዊና ስሜታዊ ዕድገት የሚከሰትበት፣ ትኩረት ተሰጥቶ ከተሰራበት በቀጣይ ስብዕና ላይ ከፍተኛ አዎንታዊ አስተዋጽዖ ያለውና የሕይወት ዘመን ማንነት መሠረት የሚጣልበት ወሳኝ የእድገት ደረጃ ነው፡፡ በዚህ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሕጻናት ቀሪው የሕይወት ዘመናቸው ስኬታማ ይሆን ዘንድ መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸው በበቂ ሁኔታ ለማሟላትና ለመልካም ዕድገታቸው አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን ማግኘት አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ሕጻናት ከማናቸውም አካላዊ፣ አዕምሮአዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ ማሕበራዊና ስሜታዊ ዕድገቶቻቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከሚያስከትሉ ሁኔታዎች ጥበቃ ሊደረግላቸውና ተገቢው ፍቅርና ክብካቤ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡

ሀገራችን እያስመዘገበችው ባለው ሁለንተናዊ እድገት በሕጻናት ሕይወት ዙሪያ የተሻሉ ለውጦች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየታዩ ቢሆንም አሁንም ምላሽ ያላገኙ በርካታ ጉዳዮች አሉ፡፡ በተለይም በሕጻናት አስተዳደግ ዙሪያ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ በመሆኑ፤ በሕጻናት ላይ የሚፈፀሙ በርካታ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መኖራቸው፤ በዕድገት ደረጃው ለሕጻናት ሊሰጡ የሚገቡ የቅድመ ልጅነት አገልግሎቶች ያልተስፋፉ መሆናቸው፣ ምቹና ተስማማሚ መኖሪያ አካባቢ መፍጠር ያልተቻለ መሆኑ፣ የተጠናከረ የሕጻናት ጥበቃ ሥርዓት ባለመዘርጋቱና በሌሎች ተመሳሰይ እጥረቶች ምክንያት በቅድመ ልጅነት ዘመን ውስጥ የሚገኙ ሕጻናት ተገቢው አያያዝ ያልተደረገላቸው፣ እንዲሁም ባልተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ በመሆናቸው ለተለያዩ ችግሮችና ጥቃቶች ተጋላጭ ናቸው፡፡

መንግስት በ2009 ዓ.ም ተግባራዊ መደረግ በጀመረው ብሄራዊ የሕጻናት ፖሊሲ መሰረት የሕጻናትን መብትና ደህንነት በማክበር፣ በማስከበርና ፍላጎታቸውን በማሟላት ረገድ እየወሰደ ያለውን እርምጃ ይበልጥ ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ በሕጻናት መልካም አስተዳደግና ስብዕና ግንባታ የቤተሰብ፣ ማህበረሰብንና የመንግስትን ሚና ለማሳደግ ተችሏል፡፡

በመሆኑም ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግና የሀገራችን ሕጻናት የቅድመ ልጅነት ዘመን በአግባቡ የሚያሳልፉበትን ሁኔታ በማመቻቸት መልካም ሰብዕና የተላበሰ ዜጋ ማፍራት ይቻል ዘንድ በተሻሉ የሕጻናት አስተዳደግ ዘዴዎች የቤተሰብ፣ የተንከባካቢዎችና መምህራን ክህሎት ማሳደግ፣ የማህበረሰቡን ሚና ማጎልበት፣ ምቹና ተስማሚ አካባቢን መፍጠር፣ የሕጻናት ጥበቃ ሥርዓትን ማጠናከር፣ ለሕጻናት መልካም ዕድገት አስተዋፆ ያላቸው አገልግሎቶችን ማስፋፋት የመሳሰሉት ሥራዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚከናወኑ በመሆናቸው ሁሉንም ባለድርሻ አካላት የቅድሚያ አጀንዳ በማድረግ ለስኬታማነቱ በተቀናጀ መልኩ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

**ዶ/ር ኤርጎጌ ተስፋዬ (ፒ. ኤች. ዲ)**

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር



# ይዘት ገጽ


| | |
|---|---|
| መግቢያ | 1 |
| **ክፍል አንድ** | **1** |
| 1. የቅድመ ልጅነት ዘመን ምንነትና ፋይዳው | 1 |
| 1.1. የቅድመ ልጅነት ዘመን (Early Childhood) | 1 |
| 1.2. የቅድመ ልጅነት ዘመን እድገትና ትምህርት (ቅልዘእት) መዋዕለ ንዋይ ፍሰት ፋይዳ | 1 |
| 1.3. የቅድመ ልጅነት ሁለንተናዊ እንክብካቤ ማዕቀፍ | 2 |
| **ክፍል ሁለት** | **4** |
| 2. የፖሊሲማዕቀፉን ማሻሻል አስፈላጊነት፣መሰረታዊ እሳቤዎች፣ ራዕይ፣ዓላማና መርሆዎች | 4 |
| 2.1. የፖሊሲ ማዕቀፉን ማሻሻል አስፈላጊነት | 4 |
| 2.2. መሠረታዊ ዕሳቤዎች | 4 |
| 2.3. ራዕይ | 5 |
| 2.4. ተልዕኮ | 5 |
| 2.5. ዓላማ | 5 |
| 2.6. የፖሊሲ ማዕቀፍ መርሆዎች | 5 |
| 2.7. የተፈፃሚነት ወሰን | 5 |
| **ክፍል ሦስት** | **6** |
| 3. የፖሊሲማዕቀፉ የትኩረት አቅጣጫዎችና የማስፈጸሚያ ስልቶች | 6 |
| 3.1. የጤና፣ ስርዓተ-ምግብና የቅድመ ማነቃቂያ አገልግሎት (ከቅድመ ወሊድ እስከ 3+ ዓመት) | 6 |
| 3.2. የቅድመ ልጅነት ዘመን ትምህርት (4-6 ዓመት) | 7 |
| 3.3. የህፃናት መብት ጥበቃና ደህንነትን ማጎልበት | 9 |
| 3.4. ምላሽ ሰጭ የህፃናት እንክብካቤ | 10 |
| **ክፍል አራት** | **12** |
| 4. ማስፈፀሚያ ማዕቀፎች | 12 |
| 4.1. ተቋማዊ አቅምን ማጠናከር | 12 |
| 4.2. የአሰራር ማዕቀፍ | 12 |
| 4.3. የፋይናንስ ምንጭ | 12 |
| 4.4. የክትትልና ግምገማ አሰራር ማጠናከር | 12 |
| **ክፍል አምስት** | **13** |
| 5. በቅልዘእት አገልግሎት አቅርቦት የባለድርሻ አካላትና አጋሮች ሚናና ኃላፊነት | 13 |
| 5.1. የባለድርሻ አካላት ተግባራትና ኃላፊነት | 13 |
| 5.2. የአጋሮች ተግባራትና ኃላፊነት | 15 |
| የ ቅልዘእት (Early Childhood Development & Education) መዋቅር፣ አስተዳደር እና ቅንጅት | 17 |

# መቅድም

የቅድመ ልጅነት ዘመን በሰው ልጅ የህይወት ዑደት ውስጥ በቀጣይ የህይወት ዘመናት ብሩህና አምራች ዜጋን ከማፍራት አኳያ በጣም ወሳኝነት አለው። ይህንንም ለማሳካት ከፍተኛ የሆነ የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት እንደሚያስፈልገው ይታመንበታል። በቅድመ የልጅነት ዘመን በርካታ የእድገት ለውጦች የሚከሰቱበትና ለህፃናቱ የወደፊት ሕይወታቸው ስኬታማነት መሠረት የሚጣልበት ነው። እንደ ሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የቅድመ ልጅነት ዘመን ከጽንሰት እስከ 6 ዓመት ያለውን የዕድገት ዘመን የሚይዝ ሲሆን ፈጣን የሆነ አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ የቋንቋ፣ የማኅበራዊ እና ስሜታዊ ዕድገት የሚከናወንበት ጊዜ ነው። በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ በርካታ የዕድገት ለውጦች የሚከሰቱበትና ለህፃናቱ የወደፊት ሕይወታቸው ስኬታማነት መሠረት የሚጣልበት ወቅት ነው። በተለይም የመጀመሪያዎቹ ሶስት ዓመታት ወሳኝና አእምሮ ከመቼውም ጊዜ በላይ እጅግ ከፍተኛ በሆነ ፍጥነት የሚያድግበት ጊዜ ነው።

በዚህ ፈጣን የዕድገት ለውጥ ወቅት ለህፃናት የተሻለ ምግብ፣ የጤና አገልግሎት፣ ሁለንተናዊ እንክብካቤና የትምህርት እድል መስጠት አለመቻል ህፃናት ምርታማ ዜጋ የመሆን፣ የተሻለ ህይወት የመምራት እድላቸውንና በአጠቃላይ ለሀገራቸው ዕድገት የሚያበረክቱትን አስተዋፅዖ ውስን ያደርገዋል። ይህንን ግንዛቤ ለማስጨበጥ ለወላጆች/አሳዳጊዎችና ለተንከባካቢዎች ትኩረት በመስጠት ሊሰራበት ይገባል።

ልጆች በእድሜያቸው መድረስ ከሚገባቸው የእድገት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ደህንነቱ የተጠበቀ ምቹ አካባቢ፣ የጤና አገልግሎት ፣ በቂና የተመጣጠነ ምግብ ፣ ቀዳሚ ማነቃቃት፣ የቅድመ አንደኛ ክፍል ትምህርት እድልና ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል። ይህንንም ለማሟላት የበርካታ ባለድርሻ አካላትን ትብብርና የቅንጅት ሥራ ይጠይቃል።

በሀገራችን የቅድመ ልጅነት ዘመን ዕድገትና ትምህርት በፖሊሲ ማዕቀፍ ደረጃ ትኩረት አግኝቶ የተጀመረው ከ2005 ዓ.ም. ወዲህ ሲሆን በቅድመ ልጅነት ዘመን ዕድገትና ትምህርት ረገድ ሁለንተናዊ የሕፃናት እንክብካቤ በጤና ፣ በትምህርትና ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ ስራዎች ሲሰሩ የቆዩ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ የህፃናት ሁለንተናዊ ዕድገት በሚፈለገው ደረጃ ሊሳካ አልቻለም። ሆኖም ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ በአንፃራዊነት አበረታች ለውጦች ተመዝግበዋል።

ለአብነት፣ የቅድመ አንደኛ ትምህርት መርሃ ግብር  በንዑስ ዘርፉ በአፀደ ሕፃናትና በሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ እነዲካተት የተደረገ ሲሆን ይህ በማይቻልባቸው አካባቢዎች በህፃን ለህፃን የትምህርት አቅርቦት ስልት እንዲሁም በተፋጠነ የትምህርት ቤት ዝግጁነት መርሃ-ግብር የቅድመ አንደኛ ትምህርት እንዲያገኙ ተደርጓል።

በዚሁ መሰረት የትምህርት ጥራትና የተደራሽነት ችግሮች እንዳሉ ሆነው የቅድመ አንደኛ ክፍል ትምህርት አጠቃላይ የተሳትፎ ምጣኔ በፖሊሲ ማዕቀፍ ተቀርፆ ስራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ በፊት ከነበረበት 4.2 በመቶ በ2012 ዓ.ም. ወደ 45.4 በመቶ ከፍ ማለት ችሏል።

ከዚህ በፊት የነበረውን የቅደመ ልጅነት ዘመን እድገትና ትምህርት ፖሊሲ ማዕቀፍ ከአለም አቀፍ የቅድመ ልጅነት ዘመን ዕድገትና ትምህርት ፕሮግራም እሳቤዎች ጋር  ለማጣጣም   እና በሀገር አቀፍ ደረጃ  ከተከለሱ ፖሊሲዎች ጋር አብሮ ለማስኬድና ወቅታዊ ለማድረግ መከለስ በማስፈለጉ ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ጤና ሚኒስቴር፣ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ፣ ገንዘብ ሚኒስቴር፣ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ ውኃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ ሰላም ሚኒስቴር፣ ፍትህ አካላት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ሴቭ ዘችልድረን፣ ዩኒሴፍ፣ ወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያና ዩኤስ አይድ ድርጅቶች ጋር በመሆን ሲሰራበት የነበረውን የፖሊሲ ማዕቀፍ በተለያየ ወቅት ረጅም ጊዜ በመውሰድ እንዲከለስና እንዲተች ከተደረገ በኋላ ለከፍተኛ አመራሮች በማቅረብ እንዲፀድቅ ተደርጓል። በተለይም ደግሞ የየዘርፉ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የጤና ሚኒስቴር እንዲሁም የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የፖሊሲውን ማዕቀፍ አተገባበር  በመሪነት ክትትልና ግምገማ እንደሚያደርጉ ታምኖበታል።

በመሆኑም የልጆችን አካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ ስሜታዊ እና ማህበራዊ የተሟላ እድገት ለማፋጠንና ለማበልጸግ ዘርፈ ብዙ የቅንጅት ሥራዎች መተግበር ይኖርባቸዋል። የፖሊሲው ማዕቀፍና ማስተግበሪያው በሀገሪቱ እንዲኖሩ መደረጉ የመላ ህፃናትን ህይወት ሊለውጥ ይችላል ተብሎ ታምኖበታል።

# ክፍል አንድ

# መግቢያ

## 1. የቅድመ ልጅነት ዘመን ምንነትና ፋይዳው

### 1.1. የቅድመ ልጅነት ዘመን (Early Childhood)

የቅድመ ልጅነት ዘመን ከቅድመ ወሊድ እስከ ስድስት ዓመት ያለውን የእድገት ዘመን የሚይዝ ሲሆን ፈጣን የሆነ አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ስነልቦናዊ፣ የቋንቋ፣ ማኅበራዊና እና ስሜታዊ እድገት የሚከናወንበት ጊዜ ነው። ይህ የእድሜ ክልል በርካታ የእድገት ለውጦች የሚከሰቱበትና ለህፃናቱ የወደፊት ሕይወታቸው ስኬታማነት መሠረት የሚጣልበት ነው። በተለይም የመጀመሪያዎቹ ሶስት ዓመታት ለአእምሮ እድገት እጅግ በጣም ወሳኝና አእምሮ ከመቼውም ጊዜ በላይ እጅግ ከፍተኛ በሆነ ፍጥነት የሚያድግበት ጊዜ ነው።

ይህ የቅድመ ልጅነት ዘመን ለወደፊት ጤናማ፣ አምራች፣ ብቁ፣ መልካም ሥነ-ምግባር የተላበሰና ኃላፊነትን መሸከም የሚችል ዜጋን ለማፍራት ተገቢውን ትኩረት ሰጥተን ልንሠራበት የሚገባ የእድሜ ክልል ነው።

በዚህ ጊዜ ልጆች በእድሜያቸው መድረስ ከሚገባቸው የእድገት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ደህንነቱ የተጠበቀ ምቹ አካባቢ፣ የጤና አገልግሎት፣ በቂና የተመጣጠነ ምግብ፣ ቀዳሚ ማነቃቃት፣ የቅድመ አንደኛ ክፍል ትምህርት እድልና ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል።

### 1.2. የቅድመ ልጅነት ዘመን እድገትና ትምህርት መዋዕለ ንዋይ ፍሰት ፋይዳ

በቅድመ ልጅነት ዘመን የሚደረጉ እንክብካቤዎችና ድጋፎች በሌላ የእድገት ዘመን ወቅት ከሚደረጉ ስራዎች ሁሉ የበለጠ አዎንታዊ ተጽዕኖ አላቸው። በተለይም ከቅድመ ወሊድ ጀምሮ ባሉት የመጀመሪያዎቹ ሶስት ዓመታት ውስጥ የሚተገበሩ የህፃናት ፕሮግራሞች በቀጣይ የህይወት ዘመን ውስጥ ከሚሰሩ ስራዎች የበለጠ ውጤታማና አዋጪ ናቸው። የቅድመ ልጅነት ዘመን እድገትና ትምህርት በሚያተኩሩ ኘሮግራሞች ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ከሚያስገኘው በርካታ ጥቅሞች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. ለአደጋ ተጋላጭና ልዩ ፍላጐት ያላቸው ሕፃናትን በመለየትና ፈጥኖ ድጋፍ በማድረግ ለህጻናቱ ሁለንተናዊ እድገት የተሻሉ ዕድሎችንና ሁኔታዎችን መፍጠር ያስችላል።

ለ. የቅድመ አንደኛ ትምህርትን ተደራሽ በማድረግ የመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ተሳትፎን በፍትሐዊነት ለማሳደግ ይረዳል።

ሐ. የቅልዘእት ፕሮግራምን በጥራት ተደራሽ ማድረግ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ይህም ከጅምሩ ሁለንተናዊ እድገታቸዉ የተረጋገጠ ሕፃናት ስለሚሆኑ በትምህርታቸው ውጤታማና አምራችና ብቁ ዜጋ ሆነው ያድጋሉ።

መ. በሀገርና በቤተሰብ ደረጃ ወጪን ይቀንሳል፤ በሚገባ ክብካቤ ያገኙ ሕፃናት ጤናማና በትምህርታቸው ውጤታማ ይሆናሉ፣ ይህም ትምህርት የሚያቋርጡትንና ክፍል ደጋሚ ተማሪዎችን ቁጥር ለመቀነስ ያስችላል።

ሠ. ጥራት ያለው የቅድመ ልጅነት ዘመን እድገትና ትምህርት አገልግሎት በሚገባ ያገኙ ሕፃናት ጤናቸው የተጠበቀና በትምህርታቸው የተሻለ ውጤት ስለሚኖራቸው ወደፊት የተሻለ የሥራ ዕድልና የተሻለ የኑሮ ደረጃ ይኖራቸዋል። በዚህም ድህነትን ይቀንሳል፣ የወላጅና የህብረተሰብ አቅምን የማጎልበት ዕድል ይፈጥራል።

ረ. በቅድመ ልጅነት ዘመን ላይ መዋዕለ ንዋይን ማፍሰስ ልጆች በጥሩ ስነምግባር እንዲቀረፁ ከማድረጉም ባሻገር ለራሳቸው፣ ለቤተሰቦቻቸውና፣ ለማህበረሰቡ በአጠቃላይ ለሀገራቸው ትልቅ ዋጋ አለው።

## 1.3. የቅድመ ልጅነት ሁለንተናዊ እንክብካቤ ማዕቀፍ

የቅድመ ልጅነት ሁለንተናዊ እንክብካቤ ማዕቀፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀርፆ በመተግበር ላይ ይገኛል። ህፃናት ተገቢውን እንክብካቤ አግኝተው ያድጉ ዘንድ በወላጅ፣በማኅበረሰብና በተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ባለድርሻ አካላት መተግበር የሚገባቸውን የተለያዩ ፕሮግራሞች የያዘ ማዕቀፍ አዘጋጅቶ መተግበር ተገቢ ይሆናል። ሁለንተናዊ የቅድመ ልጅነት እንክብካቤ ጤናማነት፣ የተመጣጠነ ምግብ፣ የሕፃናት ደህንነትና ጥበቃ፣ ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ፣ ቀዳሚ የመነቃቃት፣ የመጫወትና የመማር ወሳኝ ዘርፎች የሚያካትት ማእቀፍ ሲሆን በየዘርፉ ያሉት ነባራዊ ሁኔታዎች እንደሚከተለው ቀርቧል።

**ጤናማነት፡-** የቅድመ ልጅነት እንክብካቤን በተሳካ ሁኔታ መተግበር ይቻል ዘንድ የሕፃናትን ሁለንተናዊ ጤንነትንና የወላጆችና ተንከባካቢዎች አዕምሯዊ ጤንነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የሕፃናትን፣ የወላጆችንና ተንከባካቢዎችን ጤና ለመጠበቅና ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ በሽታን ለመከላከል፣ ለማከምና ጤናን በተገቢው ሁኔታ ለማስተዋወቅ የተለያዩ ፕሮግራሞችና ስትራቴጂዎች እየተተገበሩ ይገኛሉ።

በኢትዮጵያ መለስተኛ ስነ-ህዝብና ጤና ጥናት መረጃ /እ.ኤ.አ.2019/ መሰረት የእናቶች ቅድመ- ወሊድ አገልግሎት 73% የደረሰ ሲሆን በጤና ተቋም የሚወልዱና የድህረ-ወሊድ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ እናቶች በቅደም ተከተል 49.8% እና 34% ብቻናቸው። የሞት ምጣኔን በተመለከተ ኢትዮጵያ በምዕተ-ዓመቱ የልማት ግብ ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ህፃናትን ሞት ለመቀነስ የተያዘውን ዕቅድ ከተቀመጠው ጊዜ አስቀድማ ማሳካት የቻለች ቢሆንም አሁንም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ ጨቅላ ህጻናት ይሞታሉ። ስለሆነም አብዛኞቹ የሕፃናት ጤና ፕሮግራሞች ሕፃናትን ከሞት የማትረፍ ከዚያም በአካላዊ ጤንነት እና እድገት ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው የማሕበራዊ፣ ስነልቦናዊ፣ አእምሯዊና የተግባቦት ክህሎቶች እድገትና ብስለት ላይ ብዙም ስራ ሲሰራ አይስተዋልም።

**የተመጣጠነ ምግብ፡-** ኢትዮጵያ የእናቶችን፣ የሕፃናት እና የአፍላ ወጣቶች የስነ-ምግብ ችግር ለመቅረፍ ብሔራዊ የስነ-ምግብ ፕሮግራም በመቅረጽ፣ መመሪያዎችንና የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ መሣሪያዎችን በማዘጋጀት ተግባራዊ በማድረግ ላይ ትገኛለች። ይህ በእንዲህ እንዳለ የዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥና የስነ-ምግብ ስርዓትን ለመዘርጋት የገጠርና የከተማ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞች እየተተገበሩ ይገኛሉ፡ ፡ይሁን እንጂ እነዚህ የሴፍቲኔት ፕሮግራሞች በልየታ የሚተገበሩ በመሆናቸው ለሁሉም ሕፃናት ተደራሽ አይደሉም።

የኢትዮጵያ መለስተኛ ስነ-ህዝብና ጤና ጥናት መረጃ /እ.ኤ.አ. 2019/ እንደሚያሳየው የተመጣጠነ ምግብ እጥረት በሕፃናት ላይ ከፍተኛ ሲሆን በተለይም እድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት መካከል 37% የመቀንጨር ችግር ይታይባቸዋል። በተጨማሪም በ 6 ወር ዕድሜ ላይ ከሚገኙ ሕፃናት መካከል የእናታቸውን ጡት ብቻ ተመግበው ያደጉት 58% ያህሉ ብቻ ናቸው።በሌላ በኩል በቤት ውስጥ በቂ እንክብካቤና የአመጋገብ ችግር፣ የተለያዩ ኢንፌክሽኖች፣ በቂ ንፅህና አለመኖር፣ የእናቶች የተመጣጠነ ምግብ እጦት፣ የግልና የአካባቢ ንጽህና ችግሮች፣ ልጆችን እያጫወቱና እያነጋገሩ ለመመገብ የእናቶች ጊዜ ማጣት ደግሞ ተጨማሪ ለምግብ እጥረት የሚያጋልጡ ተግዳሮቶች ናቸው።

**የሕፃናት ደህንነትና ጥበቃ፡-** የሕፃናት ደህንነትና ጥበቃ ለሕፃናት ሁለንተናዊ ዕድገት ወሳኝ ሲሆን የሁሉንም ባለድርሻ አካላትን የተቀናጀ ጥረት የሚጠይቅ ነው። በኢትዮጵያ የሕፃናት ደህንነትና ጥበቃን ለማረጋገጥ እየተተገበሩ ካሉት ተግባራት ውስጥ የልደት ምዝገባ፣ የሕፃናት መብትና ደህንነት ጥበቃ፣ ንፅህናው የተረጋገጠ የውኃ አቅርቦት፣ የአካባቢን ደህንነት ጥበቃና ብክለትን መከላከል ተጠቃሽ ናቸው።

የሕፃናት ልደት ምዝገባ አገልግሎት ከ2008 ዓ.ም. ጀምሮ በመካሄድ ላይ ሲሆን በ2012 ዓ.ም በህይወት ከተወለዱ ሕፃናት ውስጥ የተመዘገቡት 3 በመቶ ያህሉ ብቻ ናቸው።መዋቅራዊ አደረጃጀቱ በቂ ትኩረት ተሰጥቶት በሚፈለገው ደረጃ ባለመጠናከሩ እንዲሁም የማህበረሰቡ ስለ ሕፃናት ልደት ምዝገባ ጠቀሜታያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑ ለአፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆን እንደ ምክንያት ይጠቀሳሉ።

ሕፃናት ለተለያዩ ጥቃቶችና ብዝበዛዎች ተጠቂዎች ሲሆኑ ከሚፈፀሙባቸው ጥቃቶችና ብዝበዛዎች ውስጥ አካላዊ ቅጣት፣ ቸልታ አያያዝ፣ ወሲባዊ ትንኮሳ፣ ግድያ፣ ሕፃናትን በልመና ተግባር ማሰማራት፣ ከአቅማቸው በላይና ለረጅም ሰዓት ማሰራትን (ጉልበት ብዝበዛ) መጥቀስ ይቻላል። በተጨማሪም በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ በርካታ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ያሉ ሲሆን በእነዚህም አስከፊ ድርጊቶች ምክንያት ሕፃናት ዘላቂ ለሆኑ አካላዊ፣ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ጉዳቶችና ለሞትም ጭምር ይዳረጋሉ።

በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ከሚገኙ ሕፃናት መካከል በቅድመ ልጅነት ዘመን እድሜ ላይ የሚገኙ ሕፃናት የበለጠ ተጋላጭ ናቸው። ሆኖም የሕፃናቱን ችግር ለመቅረፍ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን በሟሟላት በዘላቂነት ድጋፍ አግኝተው የሚያድጉበት ሁኔታን መፍጠር አልተቻለም። በዚህ ረገድ ባለድርሻ አካላትም በተቀናጀ አግባብ መስራት ባለመቻላቸው የተገኘው ውጤት ዝቅተኛ ነው።

ለሕፃናት ጤናማ ሁለንተናዊ እድገት ምቹ አከባቢ ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ አስተዋፅኦ አለው። ነገር ግን የመዝናኛ፤ የመጫወቻና የስብዕና ግንባታ ማዕከላት፣ የሕፃናት ማቆያዎች እንዲሁም ለሕፃናት እድገት አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶች በሁሉም አካባቢዎች አልተስፋፉም፡ ፡በተጨማሪም ትምህርት ቤቶችና ሌሎች አገልግሎት መስጫ ተቋማትም የሕፃናቱን ፍላጎት ያሟሉ ናቸው ማለትአይቻልም።

**ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ፡-** ወላጆች፣ አሳዳጊዎችና ተንከባካቢዎች ለሕፃናቱ የሚሰጡት እንክብካቤ የሕፃናቱን ፍላጎት መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡ ፡ሕፃናት በተለይም በጨቅላነት የዕድሜ ደረጃ የሚገኙት ሀሳባቸውን በንግግር መግለጽ ስለማይችሉ ፍላጎቶቻቸውን ለመግለጽ ወይም ችግር ሲያጋጥማቸው የተለያዩ ምልክቶችን ያሳያሉ። በመሆኑም በቅርብ ያሉ ተንከባካቢዎች የሕፃናቱን ፍላጎት በመረዳት ፈጣን፣ ተገቢና ፍቅር የተሞላበት ምላሽ ሊሰጡ ይገባል።ይህም በሕፃናቱ ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖዎችን ያሳርፋል።

በአገራችን በልጅ አስተዳደግ ዙሪያ ያለው ግንዛቤና ክህሎት አነስተኛ በመሆኑ፣ የሕፃናት ማቆያዎች ያልተስፋፉ በመሆናቸውና ወላጆች/ አሳዳጊዎች ቤተሰባቸውን ለመደገፍ በተለያዩ ሥራዎች ስለሚጠመዱና በቂ ጊዜ ለሕፃናቱ መስጠት ስለማይችሉበርካታ ሕፃናት ይህንን እንክብካቤ በተሟላ ሁኔታ እያገኙ አይደለም።

**ቀዳሚ የመነቃቃት፤ የመጫወትና የመማር እድል፡-** ሕፃናት ከተወለዱበት ጊዜ አንስቶ የመነቃቃት (በአእምሮ እና በአካል)፣ የመጫወት፣ የመማርና የተግባቦት እድል ሊመቻችላቸው ይገባል። ሆኖም ቀዳሚ መነቃቃት ላይ መረጃ የሚሰጡና ለማማከር የሚረዱ የስራ መርጃዎች ተዘጋጅተዉ ጥቅም ላይ አልዋሉም። በተጨማሪም ለሕፃናት ቀዳሚ ማነቃቂያ፣ መማር፣ መጫወትና ተግባቦት የሚረዱ ሥራዎች በአግባቡ ተለይተው በተቀናጀ መልኩ በተለያዩ የፕሮግራም ዘርፎች በሕብረተሰቡ ውስጥ እየተተገበሩ አይደለም።

በሀገራችን የቅድመ አንደኛ ትምህርት በፖሊሲ ደረጃ ትኩረት አግኝቶ የተጀመረው ከ2005ዓ.ም. ወዲህ ሲሆን በነዚህ ዓመታት በአንፃራዊነት አበረታች ለውጦች ተመዝግበዋል። በንዑስ ዘርፉ በአፀደ ሕፃናትና በሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የቅድመ አንደኛ ክፍል መርሃ ግብር እንዲኖራቸውና ከላይ በተገለፁት በሁለቱም ፕሮግራሞች መስጠት በማይቻልባቸው አካባቢዎች በሕፃን ለሕፃን የትምህርት አቅርቦት ስልት እንዲሁም በተፋጠነ የትምህርት ቤት ዝግጁነት መርሃ ግብር የቅድመ አንደኛ ትምህርት እንዲያገኙ ተደርጓል። በዚሁ መሰረት የትምህርት ጥራትና የተደራሽነት ችግሮች እንዳሉ ሆነው የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርትአጠቃላይ የተሳትፎ ምጣኔ በ2012 ዓ.ም. ዓመታዊ የትምህርት ስርዓት መረጃ 45.4 በመቶ መድረሱን አመልክቷል።

በአጠቃላይ በቅድመ ልጅነት ዘመን ዕድገትና ትምህርት ረገድ ሁለንተናዊ የሕፃናት እንክብካቤ በጤና፣ በትምህርትና በማህበራዊ አገልግሎት ዘርፍ ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ ስራዎች ሲሰሩ የቆዩ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ የሕፃናት ሁለንተናዊ ዕድገት ማረጋገጥ በሚፈለገው ደረጃ ውጤታማ አልነበረም። በመሆኑም የልጆችን አካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ የቋንቋ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ የተሟላ እድገት ለማፋጠንና ለማበልጸግ ዘርፈ ብዙ የቅንጅት ሥራዎች መተግበር ይኖርባቸዋል።

# ክፍል ሁለት

## 2. የፖሊሲ ማዕቀፉን ማሻሻል አስፈላጊነት፣መሰረታዊ እሳቤዎች፣ ራዕይ፣ዓላማና መርሆዎች

### 2.1. የፖሊሲ ማዕቀፉን ማሻሻል አስፈላጊነት

በሀገራችን የቅድመ ልጅነት ዘመንን ስኬታማ ለማድረግ በማለም በ2005 ዓ.ም. የቅድመ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት ብሔራዊ የፖሊሲ ማዕቀፍ፣ ስትራቴጂና መመሪያ በማዘጋጀት ወደ ስራ መገባቱ ይታወቃል። ሆኖም ግን የፖሊሲውን ማዕቀፍ ከወቅታዊ፣ ዓለምአቀፋዊ የቅድመ ልጅነት ዘመን እድገትና ትምህርት እና ከአገራችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም መከለስ አስፈልጓል። በዚህም መሰረት መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ተጨማሪ ዋና ዋና የፖሊሲ የትኩረት አቅጣጫዎችን በማካተት ጥራቱን የጠበቀና የሕፃናትን ሁለንተናዊ እድገት ትኩረት የሚሰጥና የቅልዘእት አገልግሎት ተደራሽነት ለማስፋት የሚያስችል የፖሊሲ ማዕቀፍ በማድረግ ተከልሷል።

### 2.2. መሠረታዊ ዕሳቤዎች

ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የህፃናት መብቶች ስምምነት እና የአፍሪካ የህፃናት መብትና ደህንነት ቻርተር ሰነዶችን ተቀብላ በማፅደቅ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት የሀገሪቱ የህግ አካል እንዲሆኑ ተደንግጓል። ይህንንም መነሻ በማድረግ የሕፃናትን መብት ለማስከበርና የሕፃናትን ተጠቃሚነት ለማጎልበት የሚያስችሉ የህግ ማሻሻያዎችን በማድረግ፣ የፖሊሲ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት እና የተለያዩ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል።

በዚህም መሰረት ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ስምምነትና ሀገራዊ የሕፃናት መብት ማስጠበቂያ የሕግ ማዕቀፎችና ፖሊሲዎች በዋነኛነት እንደሚከተለዉ ተዘርዝረዋል።

**ሀ. የሕፃናት መብት ኮንቬኤንሽን (እ.ኤ.አ 1989)፡-** ስምምነቱ ሕፃናት በህግ፣ በማህበራዊ ጉዳዮችና በትምህርት ተገቢው ጥበቃና አገልግሎት እንዲሚያገኙ ይደነግጋል።

**ለ. የዘላቂ የልማት ግቦች (እ.ኤ.አ 2015)፡-** ግብ 4 ስር ንዑስ ክፍል 4.2 እና በግብ 3 ስር ንዑስ ክፍል 3.2 እንደተጠቀሰው ሁሉም ህፃናት ጥራት ያለው እንክብካቤና የቅድመ አንደኛ ትምህርትና ጤነኛ ሆነው የማደግ መብት እንዳላቸው ያመለክታል።

**ሐ. አጀንዳ 2063 እ.ኤ.አ፡-** በሁሉም የአፍሪካ ሀገሮች ዘንድ ጥራት ያለው የቅልዘእት አገልግሎት ተደራሽ መሆን እንዳለበት ከስምምነት ተደርሷል።

**መ. የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት (1987 ዓ.ም.)፡-** አንቀጽ 36 የሕፃናት መብት መከበር እንዳለበት ዓፅንዖት ሰጥቶ ያስቀምጣል። እንዲሁም በአንቀፅ 90 ህፃናት የትምህርት፣ የጤና፣ የማህበራዊ አገልግሎቶችን ማግኘት እንዳለባቸው ያስቀምጣል።

**ሠ. ብሔራዊ የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ (2007 ዓ.ም.)፡-** ፖሊሲው የሕፃናት የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ችግሮችንበመፍታት ተጋላጭነታቸውን ለመቀነስ አቅጣጫ አስቀምጧል።

**ረ. ብሔራዊ የሕፃናት ፖሊሲ (2009 ዓ.ም.)፡-** ፖሊሲው የሕፃናት መልካም አስተዳደግና እድገት፣ በሕፃናት ላይየሚደርሱ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን መከላከል፣ ጥበቃ ማድረግና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ሕፃናት ተሃድሶ፣ ድጋፍና እንክብካቤ እንደሚያስፈልግ በግልጽ ተቀምጧል።

**ሰ. የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ (1986 ዓ.ም.)፦** የቅድመ አንደኛ ትምህርት ተቋማት ለሕፃናት ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ በማተኮር ሕፃናቱን ለመደበኛ ትምህርት ማዘጋጀት እንዳለባቸው ይጠቁማል።

**ሸ.ብሔራዊ የጤና ፖሊሲ (2011 ዓ.ም.)፦** የጤናው ዘርፍ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ደግሞ ለእናቶችና ሕፃናት ትኩረት እንደሚሰጥ ይጠቁማል።

**ቀ. የምግብ እና ስርዓተ ምግብ ፖሊሲ (2011 ዓ.ም.)፦** የእናቶች እና ሕፃናት ስርዓተ ምግብ ማሻሻል ላይ ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

**በ. የአፍሪካ የህፃናት መብትና ደህንነት ቻርተር (1982/በ1992 )፦** ቻርተሩ የአፍሪካ ሕፃናት መብትና ደህንነትን ለማስጠበቅ ተገቢ የተባሉ እርምጃዎች ሁሉ እንደሚወሰዱ ይገልፃል።

## 2.3. ራዕይ

እያንዳንዱ ከ0-6 አመት እድሜ ክልል ውስጥ ያሉት የኢትዮጵያ ሕፃናት ጥራቱን የጠበቀና ሁሉን አቀፍ የቅድመ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት አገልግሎት በማግኘት፣ መልካም ስብዕና የተላበሱ፣ ሙሉ አቅማቸውን መጠቀም የሚችሉ፣ ጤናማና አምራች ዜጋ ይሆናሉ።

## 2.4. ተልዕኮ

1. ሁሉን አቀፍ፣ የተቀናጀ፣ ጥራት ያለው፣ ከአካባቢው ጋር የተጣጣመ የተሟላ የቅድመ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት አገልግሎትን በመስጠት የሕፃናቱን ሁለንተናዊ ዕድገት ማበልፀግ፤

2. የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ህጻናት ባህልና ቋንቋን ባከበረና ባረጋገጠ መልኩ የሕፃናቱ እምቅ ችሎታና ሙሉ አቅም እንዲያድግ ማድረግ፤

3. የሁሉንም ሕፃናት መብቶችና ደህንነት እንዲረጋገጥ ማድረግ፤

4. ጥራት ያለው አገልግሎት ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ለሕፃናት እንዲሰጥ ማድረግ።

## 2.5. ዓላማ

በውጤታማ አጋርነትና በአቅም ግንባታ ኘሮግራሞች ላይ በመመሥረት ከቅድመ ወሊድ እስከ ስድስት ዓመት ያሉ የኢትዮጵያ ሕፃናት ጥራት ያለው የቅድመ ልጅነት ዘመን እድገት፣ መዳበርና ትምህርት አገልግሎት አግኝተው ጥሩ የሕይወት ጅማሮ እንዲኖራቸው በማስቻል የአካላዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ አእምሮአዊ እና ማህበራዊ እድገታቸው እንዲጎለብት ለማድረግ ነው።

## 2.6. የፖሊሲ ማዕቀፍ መርሆዎች

ሀ. ለሕፃናት ፍላጎትና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት

ለ. ፍትሃዊና ከአድልዎ የፀዳ አገልግሎት

ሐ. የተቀናጀ ዘርፈ ብዙ ምላሽ

መ. ጨዋታን ማዕከል ያደረገ አገልግሎት

ሠ. የሕፃናት የእድሜ ደረጃንና ልዩ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ አገልግሎት

ረ. የሕፃናትና ወላጆች እንዲሁም የህብረተሰብ ተሳትፎ

ሰ. ጥራት ያለው አገልግሎትና ወጪ ቆጣቢነት

ሸ. የሀገራችንን ባህላዊ ዕሴቶች መጠበቅ

## 2.7. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ የቅድመ ልጅነት ዘመን እድገት፣ መዳበርና ትምህርት የፖሊሲ ማዕቀፍ ከቅድመ ወሊድ እስከ 6 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ህፃናት ላይ ያተኮረ ነው።

# ክፍል ሦስት

## 3. የፖሊሲ ማዕቀፉ የትኩረት አቅጣጫዎችና የማስፈጸሚያ ስልቶች

### 3.1. የጤና፣ ስርዓተ-ምግብና የቅድመ ማነቃቂያ አገልግሎት (ከቅድመ ወሊድ እስከ 3+ ዓመት)

የጤናው ዘርፍ የተለያዩ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ሁሉን አቀፍ የሆነ የእናቶችና የህፃናት፤ የአፍላ ወጣቶችና የወጣቶች ጤና፣ የምግብና ስርዓተ-ምግብ አገልግሎት ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ በማድረግ ከፍተኛ ስራ በመሰራት ላይ ይገኛል። በተለይ ደግሞ ለእናቶችና ሕፃናት ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት ከቅድመ ወሊድ እስከ 3+ ዓመት ላሉ ሕፃናትና ለወላጆቻቸው ጤናን፣ ምግብንና ስርዓተ-ምግብን በተመለከተ የተቀናጀ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል።

ይህንን የትኩረት አቅጣጫ ለማሳካት ወላጆች/አሳዳጊዎች ከልጆቻቸው ጋር እንዴት መጫወትና መነጋገር እንዳለባቸው እንዲሁም ስለ ሕፃናት እንክብካቤ፣ አያያዝና አስተዳደግ በጤና ባለሙያዎች የምክር አገልግሎትና ትምህርት ሲሰጣቸው በየጤና ተቋማቱ ወይም አገልግሎቱ በሚሰጥባቸው ማእከላት ውስጥ ሕፃናት ከወላጆቻቸው ወይም ከሌሎች እኩዮቻቸውጋር የሚጫወቱባቸው በታዎችና የመጫወቻ ቁሳቁሶች በማሟላት ምቹና ተስማሚ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህ ፕሮግራም መሳካት ከጤና ባለሙያዎች በተጨማሪ በቤተሰብና በህብረተሰብ ደረጃ ትኩረት ሰጥቶ መስራትን ይጠይቃል። ስለዚህም የሚታዩትን ክፍተቶች ለመቅረፍ የሚከተሉት የጤና ግቦችና የማስፈጸሚያ ስልቶች ተነድፈዋል።

#### 3.1.1. ግቦች

ሀ. የጤናው ዘርፍ፣ የቅድመ ልጅነት እድገትና ትምህርት ፖሊሲን ማዕቀፍ መሰረት ያደረገ እና ጥራቱን የጠበቀ ሁለገብ የቅድመ ልጅነት እድገትና መዳበር አገልግሎትን ባሉት የእናቶችና ሕፃናት የጤና፣ የምግብና ስርዓተ-ምግብ፣ ተጨማሪም በሌሎች ተያያዥነት ባላቸው የጤና ፕሮግራሞች ውስጥ በማካተት በሁሉም የጤና ተቋማትና በማህበረሰብ ደረጃ ተደራሽነቱን ማረጋገጥ፤

ለ. የምግብና ስርዓተ-ምግብ አገልግሎቶች ተጠናክረውና ጥራታቸውን ጠብቀው የቅድመ ልጅነት ዘመን እድገትና መዳበር አገልግሎትን ትኩረት ባደረገ መልኩ እንዲሰጡ ማስቻል፤

ሐ. ወላጆች/አሳዳጊዎች ቅድመ ልጅነት ዘመን እድገትና መዳበር አገልግሎትን መሰረት ያደረገ በቂ እውቀት፣ ግንዛቤና አቅም አግኝተው ለልጆቻቸው ተገቢውን እንክብካቤ እንዲሰጡ ማስቻል፤

መ. ሕብረተሰቡ በቅድመ ልጅነት ዘመን እድገትና መዳበር ላይ ግንዛቤና ክህሎት ኖሮት እንዲሁም በራስ የሚተማመንና የሚወስን ሆኖ በልጆች አስተዳደግ ዙሪያ ተገቢውን ኃላፊነት እንዲወጣ ማስቻል።

#### 3.1.2. የማስፈጸሚያ ስልቶች

ሀ. የእናቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጤና እና የስርዓተ-ምግብ አገልግሎትን ከቅድመ ልጅነት እድገት/ መዳበር አገልግሎቶች ጋር በማቀናጀት ጥራት ባለው ደረጃ ለመስጠት የጤና ባለሙያዎችን አቅም የሚያጎለብቱ ፕሮግራሞች ይተገበራሉ፤

ለ. በመተግበር ላይ ካሉት የእናቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጤና፣ ምግብና የስርዓተ-ምግብ አገልግሎቶች ጋር ያልተካተቱትን የቅድመ ልጅነት እድገት/ መዳበር አገልግሎቶች ማለትም የቅድመ ማነቃቂያና ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ አገልግሎቶችን በማካተት ጥራትና ተደራሽነትን የሚያረጋግጡ ስራዎች ተቀርፀው በስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፤

ሐ. የጤና ተቋማትን ለልጆች ምቹና ተስማሚ በማድረግ ሁለንተናዊ የቅድመ ልጅነት እድገት/ መዳበር አገልግሎት እንዲሰጥባቸው ለማድረግ አስፈላጊው ግብዓት እና በጀት እንዲመደብ ይደረጋል፤

መ. ልጆች ንጽህናው በተጠበቀና ምቹ በሆነ አካባቢ ላይ እንዲያድጉና ለቅድመ ልጅነት ዘመን እድገት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር የሚያበቁ የግንዛቤ እና የክህሎት ማስጨበጫ ስራዎች ከባለድርሻ አካላት (ከሚመለከታቸው ሴክተር መ/ቤቶች) ጋር በጋራ ተቀርፀው በስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፤

ሠ. በጤና ተቋማትና በቤት ለቤት በሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች ውስጥ የእድገትና መዳበር ክትትልና ልየታ (developmental milestone screening) አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፤

ረ. የእድገት መዘግየት ላጋጠማቸው ሕፃናት አገልግሎት ወደሚያገኙበት ተቋም ለመላክ የቅብብሎሽ ሥርዓት ይዘረጋል፤

ሰ. ወላጆች/ አሳዳጊዎች የቅድመ ልጅነት ዘመን አስፈላጊነትን በበቂ ሁኔታ እንዲገነዘቡና እንዲያውቁ በማድረግ የቅድመ ልጅነት ዘመን እድገትና መዳበርን አገልግሎት መሰረት ያደረገ እንክብካቤና የልጅ አያያዝን እንዲተገብሩ የሚያስችል የምክር አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፤

ሸ. ሕብረተሰቡ የቅድመ ልጅነት ዘመን እድገትና መዳበር ላይ ግንዛቤና ክህሎት እንዲኖረው የሚያበቁ ተግባራት ተለይተው በስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።

## 3.2. የቅድመ ልጅነት ዘመን ትምህርት (4-6 ዓመት)

የቅድመ አንደኛ ትምህርት መርሀ ግብር እድሜያቸው ከ 4-6 ያሉ ሕፃናትን ጨዋታ ተኮር ያደረገ ትምህርት እንደየአካባቢ ነባራዊ ሁኔታ ተቃኝቶ በተዘጋጀሥርዐተ ትምህርት አማካይነት በተቋምና ከተቋም ውጭ የሚሰጥ መርሀ-ግብር ሲሆን ዋነኛ ዓላማውም ሕፃናትን ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሀ-ግብር ዝግጁ እንዲሆኑ ማስቻል ነው።

የቅድመ አንደኛ ክፍል ትምህርት ፕሮግራም የሚያተኩረው ጨዋታ ተኮር በሆነ የአቀራረብ ዘዴ የሕፃናቱን ሁለንተናዊ እድገት ማለትም በአዕምሮአዊ፣ በአካላዊ፣ በማህበራዊ፣ በስሜትና በግብረ ገብ የተስተካከለ የስብዕና እድገት እንዲኖራቸው ማድረግን ያለመ መርሃ-ግብር ነው። በተለይም ሕፃናት መሰረታዊ የትምህርት ክህሎቶችን (ቅድመ ንባብ፣ ጽህፈት፣ አሃዝና ስሌት)፣ የማህበራዊ (ተግባቦቶችን፣ ራሳቸውን መግለጽ፣ በጋራ መስራት፣ መከባበር)፣ የስሜት (ራስን የመቆጣጠር፣ ለሌሎች ማሰብ፣ መከባበር) እና አካላዊ እድገትን በሚያዳብር መልኩ ከሀገር በቀልና ዘመናዊ እውቀቶች ተሰናስለው / ተላብሰው / እንደየአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ በተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት በሰለጠኑ መምህራንና ምቹና ደህንነቱ በተጠበቀ ተቋም ውስጥ የሚሰጥ መርሀ ግብር ነው።

በመሆኑም የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ተፈፃሚ እንዲሆን ለማስቻልም ውጤታማ የሆነዕቅድ እና የሃብት አመዳደብ፣ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት፣ የመምህራን፣ የሞግዚቶች፣ የአመቻቾች፣ ዘርፉን የሚመሩ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የትምህርት ባለሙያዎች አሰለጣጠንና አመዳደብ፣ የወላጅና የማህበረሰብ ተሳትፎ፣ የትምህርት ጥራት፣ ተደራሽነትና ፍትሃዊነትን የማስጠበቅ ስራ ላይ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል።

### 3.2.1. ግቦች

ሀ. በቅድመ አንደኛ ትምህርት መርሃ-ግብር ሕፃናት በአካል፣ በአዕምሮ፣ በስሜት በማህበራዊ፣ በስነ-ምግባርና በባህል ታንፀው ለአንደኛ ደረጃ ትምህርትና ለዕድሜ ልክ ትምህርት ዝግጁ እንዲሆኑ ይደረጋል፤

ለ. ከ 4 እስከ 6 ዓመት ለሆናቸው ህፃናት ተደራሽ፣ ፍትሃዊና አካታች፣ የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ጥራት ያለው የትምህርት አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል በተለይም ከዚህ ቀደም የጥቅሙ ተጋሪ ላልነበሩት ሕፃናት ትኩረት ይሰጣል፤

ሐ. ለቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ውጤታማ የሆነ የመዋዕለ ንዋይ አሰባሰብ፣ የእቅድ አዘገጃጀትና ፍታሃዊ የሆነ የክፍፍል ስርዓትን ይዘረጋል፤

መ. በቅድመ አንደኛ ደረጃ ያሉት ህፃናትን ሁለንተናዊ ዕድገት፣ ፍላጎት፣ ባህል፣ ግብረገብእና ልጆችን ማዕከል ያደረገ ሥርዓተ ትምህርት ተቀርፆ ይተገበራል፤

ሠ. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ማሰልጠኛ ተቋማትን በማስፋፋት እና ያሉትንም በማጠናከር ብቁ መምህራንን፣ የትምህርት ዘርፉን የሚመሩ ባለሞያዎችን፣ ተንከባካቢዎችንና አመቻቾች ተገቢውን ትምህርትና ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፤

ረ. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጠው የቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህራን ስልጠና ከቅድመ አንደኛ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት ጋር የተጣጣመ ሆኖ እንዲተገበር ይደረጋል፤

ሰ. በቅድመ ልጅነት ዘመን እንክብካቤናትምህርት ላይ የወላጆች እና የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማስፋት በንቃት እንዲሳተፉ ይደረጋል፤

ሸ. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ለሕፃናቱ ምቹ እና ሳቢ እንዲሆኑ ይደረጋል፤

ቀ.ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ሕፃናት የተሟላና ጥራት ያለው ትምህርትን ሳይገለሉ በአከባቢ በሚገኝ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ከአቻዎቻቸው ጋር ተካተው እንዲማሩ ይደረጋል፤

በ. የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም፣ የንፁህ ውኃ አቅርቦት፣ የመጸዳጃ ቤቶች፣ የመጀመርያ ደረጃ ህክምና እርዳታ አገልግሎት እንዲኖራቸው እና በአቅራቢያ ካለ የጤና አገለግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር በቅንጅት እንዲሰሩ ይደረጋል፤

ተ. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለማስፋፋትና ተደራሽ ለማድረግ የሚሰሩ የሃይማኖትና የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

### 3.2.2. የማስፈጸሚያ ስልቶች

ሀ.ነፃና አስገዳጅ ሦስት ዓመት የቅድመ አንደኛ ክፍል ትምህርት መርሃ ግብር መዘርጋት፤

ለ. የቅድመ ልጅነት ትምህርት ጠቀሜታ፣ የሕፃናት መብትና ደህንነት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥርዓት መዘርጋት፤

ሐ. ለቅድመ ልጅነት ትምህርት ዘርፍ ተገቢውን በጀት ለመርሃግብሩ ማስፈጸሚያ እንዲመደብ ማድረግ፤

መ. ለህፃናት ተስማሚ ምቹና ከስጋት ነፃ የሆኑ የቅድመ አንደኛ ክፍል የትምህርት ተቋማት በአቅራቢያ መንደሮች መክፈት፤

ሠ. መንግሥት፣ ህብረተሰብና አጋሮች በማስተባበር ጥራት ያለውን የቅድመ አንደኛ ክፍል የትምህርት አገልግሎት በሁሉም አካባቢዎች ማዳረስ፤

ረ. ለመምህራን ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ለመለየትና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል እውቀትና ክህሎት እንዲያዳብሩ የቅድመ ሥራና የሥራ ላይ ሥልጠና መስጠት፤

ሰ. ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት ለመለየትና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችሉ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከላት ማቋቋምና ማጠናከር፤

ሸ. የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት የቅድመ አንደኛ ክፍል ትምህርት መምህራንን የሥራ ላይ ሥልጠና መርሃግብር እንዲከፍቱና እንዲጠናከሩ ማድረግ፤

ቀ. የቅድመ አንደኛ ክፍል ትምህርት አገልግሎት ለሚሰጡ ተቋማት ስታንዳርድ ማዘጋጀት፣ ለአፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤

በ. የቅድመ አንደኛ ትምህርት ተቋማት ብቃት የአፈፃፀም መለኪያ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት፤

ተ. የቅድመ አንደኛ ትምህርት የቅድመ ሥራና የሥራ ላይ ስልጠና ፕሮግራም ውስጥ የምልክት ቋንቋ፣ የብሬል፣ የንክኪ (ተክታይል) እና ሌሎች የመግባቢያ ፎርማቶች ላይ የሥልጠና ማዕቀፍ ማዘጋጀት፤

ቸ. ሕፃናትን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ማስተማር፡፡

## 3.3. የህፃናት መብት ጥበቃና ደህንነትን ማጎልበት

በቅድመ ልጅነት ዘመን የእድሜ ክልል የሚገኙ ህፃናት ከለጋነታቸው አንፃር ለተለያዩ ችግሮች ይበልጥ ተጋላጭ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ከፍተኛ አካላዊ፣ አእምሮአዊና ማህበራዊ እድገት የሚከሰትበት የእድሜ ክልል በመሆኑ ከፍተኛ ደህንነት፣ ጥበቃና እንክብካቤን የሚጠይቅ ነው። ይሁን እንጂ አብዛኞቹ የሀገራችን ህፃናት ለተለያዩ ችግሮች፣ ጎጂ-ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ቸልተኛ የሕፃናት አያያዝ፣ ጥቃቶችና ብዝበዛዎች የተጋለጡ ከመሆናቸው በተጨማሪ አብዛኛዎቹ ባልተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ የሚያድጉ ናቸው።

ይህም በአካላዊ፣ አዕምሮአዊና ማህበራዊ እድገታቸው ላይ የሚያስከትሉት አሉታዊ አስተዋፅዖ ከፍተኛ ነው። በመሆኑም ይህንን ሁኔታ በማስወገድና ምቹ አከባቢን በመፍጠር ለሁለንተናዊ እድገታቸው የሕፃናትን መብትና ደህንነትን ማረጋገጥ የሚያስችል የጥበቃ ሥርዓትን መዘርጋት የፖሊሲው ማዕቀፍ አንዱ የትኩረት አቅጣጫ ነው።

### 3.3.1. ግቦች

ሀ. ሕፃናት ዕድሜ ተኮር የሆኑ አገልግሎቶችን ማለትም ክትባቶችን፣ ዕድሜን ያማከለ ትምህርት በወቅቱ እንዲያገኙ እንዲሁም ያለዕድሜ ጋብቻን እና የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን ከመሳሰሉ ጎጂ ልማዶች እንዲጠበቁ ለማስቻል ሁሉም ህፃናት በልደት መዝገብ እንዲመዘገቡ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይሆናል።

ለ. በቤተሰብ፣ በሕፃናት ማቆያ፣ በሕፃናት ማሳደጊያና በመሳሰሉት ሁሉ የሚገኙ ሁሉም በቅድመ ልጅነት ዘመን እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት አካላዊ እና አዕምሯዊ ደህንነታቸው በሚጠበቅበት አከባቢ እንዲያድጉ ተገቢው ትምህርትና ስልጠና ይሰጣል፣ ወቅታዊ ክትትል እና ቁጥጥር ይደረጋል፤

ሐ. የሕፃናት ጥበቃ ሥርዓት እንዲጎለብት በማድረግ፣ለችግር አጋላጭ በሆነ አስቸጋሪ እና በተገለለ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሕፃናት ያሉበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ የልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት እንዲያገኙ፣ ከአደጋና ከጥቃት እንዲጠበቁ ይደረጋል፤

መ. ጥቃትና በደል ለደረሰባቸው አስፈላጊው እንክብካቤ የተነፈጋቸው ሕፃናትን ጨምሮ ፍትህ እንዲያገኙ ወቅታዊ የህግ ድጋፍ እና የህክምና/የማገገሚያ አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል።

### 3.3.2. ማስፈጸሚያ ስልቶች

ሀ. የልደት ምዝገባን በተመለከተ ለማህበረሰቡ ግንዛቤን ማስጨበጥ፣ የምዝገባ ስርዓቱን ለተገልጋይ ምቹ በማድረግ ከባለድርሻ አካላትጋር ተቀናጅቶ መስራት፤

ለ. ወላጆች/አሳዳጊዎች የክህሎት ስልጠና ወስደው ለሕፃናት ንፁህ፣ ለአደጋ የማያጋልጥ፣ ነፃ እንቅስቃሴን የማይገድብና ልጆቹ በግላቸው ዙሪያቸውን በመቃኘት እንዲመራመሩ የሚያስችል የመጫወቻ ቦታ እንዲፈጥሩ፣ የልዩ ፍላጎትላላቸው ሕፃናት አግባብ ያለው ድጋፍ እንዲያደርጉ የሚያስችል ፕሮግራም መተግበር፤

ሐ. ወላጆች ለልጆቻቸውና ለህብረተሰቡ መልካም አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ በመጀመሪያ የራሳቸውን አካላዊ እና አዕምሯዊ ደህንነት እና አጠቃላይ መረጋጋት እንዲኖራቸው የሚያግዝ ክህሎት እንዲያዳብሩ ድጋፍ ማድረግ፤

መ. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራሞችን እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በየደረጃው የማሻሻል እና የማስፋፋት ስራ ይሰራል፣ በተጨማሪም በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ሕፃናትምቹ፣ ንፁህ፣ ለአደጋ እና ጥቃት የማያጋልጥ እና ዕድሜ-ተኮር የመጫወቻ/የመማሪያ ቁሳቁስ ያለባቸው የሕፃናት መዋያዎች እንዲኖሩ ይደረጋል።ይህ ተግባር የሴፍቲኔት አገልግሎት ተጠቃሚ በሆኑ ህብረተሰቦች ውስጥም በቅንጅት ይተገበራል፤

ሠ. ህፃናት የተሟላ የማህበራዊ ደህንነት አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፤

ረ. ወላጆች/አሳዳጊዎች በተለያዩ ዘርፎች ለህጻናትና ለቤተሰብ የሚሰጡ አገልግሎቶችን እንዲጠይቁና እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ማገናኘት፣ መደገፍ እና ማበረታታት።

ሰ. ቤተሰቦች/ አሳዳጊዎች ወደ ከፋ ድህነት ውስጥ እንዳይገቡ አስፈላጊ የማህበራዊ አገልግሎት እንዲሰጣቸው ይደረጋል፤

ሸ. ሕፃናት ጥቃት፣ በደልና ብዝበዛ እንዳይደርስባቸው ይደረጋል ጥቃት ለደረሰባቸውም የማህበራዊና ስነልቦናዊ ድጋፍ እንዲሁም ፍትህ እንዲያገኙ ማድረግ፤

ቀ. ከተቋማዊ የድጋፍ አገልግሎት ይልቅ የቤተሰብና የማህበረሰብ አቀፍ የሕፃናት ድጋፍ አገልግሎቶች እንዲጠናከሩ ማድረግ፤

በ. የቅልዘእት ስልጠናን በተለይም ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ ማሳደግ እና በህጻናት ላይ የሚደርሱ ከባድ ቅጣትን/ጥቃትን መከላከልን በህጻናት እና ማህበራዊ ጥበቃ ዘርፎች ተቋማዊ በማድረግ የሰው ሃይል ልማትን ማጠናከር ።

ተ. በየወቅቱ የሚደረጉ የጤናና ማህበራዊ ኩነቶች ጥናቶች በሚሰበስቧቸው መረጃዎች ውስጥ ሕፃናት ላይ የሚደርሱ አካላዊ፣ አዕምሯዊና ወሲባዊ ጥቃቶችን እና አስፈላጊ እንክብካቤ የተነፈጉ ህፃናትን በተመለከተ እንዲያካትቱ ማድረግ፤

ቸ. የግጭት አዝማሚያ በሚታይባቸው ማህበረሰቦች ውስጥ ሰላማዊና ህጋዊ በሆነሁኔታ መተግበር የሚገባቸው የግጭት መከላከያ ዘዴዎች ተነድፈው ተግባራዊ ይደረጋሉ። በዚህም የሕፃናት ደህንነትና ምቾት ይጠበቃል፤

ነ. የሕፃናትን መብትና ደህንነት ለማረጋገጥ እንዲሁም ሕፃናትን ከእንክብካቤ እጦት፤ ከተለያዩ አደጋዎችና ጥቃቶች ለመታደግ በህጉ ውስጥ ያሉ ክፍተቶች እንዲስተካከሉ ይደረጋል።

## 3.4. ምላሽ ሰጭ የህፃናት እንክብካቤ

ወላጆች/ አሳዳጊዎች በልጆቻቸው ዕድገት ላይ ትልቅ አስተዋፅዖ ያላቸው ሲሆን በተለይም በቅድመ ልጅነት ዘመን አእምሮ ፈጣን እድገት የሚያሳይበት በመሆኑ በዚህ ወቅት በሕፃናት ላይ የሚደርሱ ችግሮች ዘላቂ የሆነ ጠባሳ ስለሚያስከትሉ ወላጆች/ አሳዳጊዎች ለሕፃናት የሚያሳዩት ፍቅርና እንክብካቤ የሕፃናቱ ልዩና መሰረታዊ ፍላጎታቸው ተሟልቶ፣ የህይወት ክህሎቶቻቸውን ጎልብቶ፣ በራስ የሚተማመኑና መልካም ስብዕና ኖሯቸው እንዲያድጉ ያስችላል። በመሆኑም የወላጆች/ አሳዳጊዎች በሕፃናት ሁለንተናዊ እድገት ዙሪያ ግንዛቤ እና ክህሎት ማሳደግ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ነው።

በኢትዮጵያ አብዛኞች ወላጆች/ አሳዳጊዎች በተደራራቢ ችግሮቹ፣ በድህነት ተፅዕኖ እንዲሁም ከግንዛቤ ጉድለት የተነሳ ማድረግ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ለማድረግ አቅም

እና ጊዜ ሲያንሳቸው ይስተዋላል። በመሆኑም የሕፃናት ፍላጎትን በወቅቱ ተረድቶ ተገቢ ምላሽ መስጠትን በተመለከተ በቂ ትኩረት ሳይሰጥ ቆይቷል። ይህ ሁኔታ ደግሞ ሕፃናት በለጋ እድሜያቸው ቸል እንዲባሉ እና ማግኘት የሚገባቸውን እንክብካቤና ፍቅር በማጣት በቀጣይ ዘመናቸው በራስ ያለመተማመን፣ የመገለል፣ የብቸኝነት፣ ከመጠን ያለፈ ራስ ወዳድነት፣ ኃላፊነት ያለ መሰማት፣ ያለ መረጋጋትና ለተለያዩ የአእምሮና የባህርይ ችግሮች ይጋለጣሉ።

በመሆኑም በሕፃናት አያያዝና አስተዳደግ የወላጅ/ አሳዳጊና የማህበረሰቡን ግንዛቤ፣ ክህሎትና አመለካከት እንዲሁም የኢኮኖሚ አቅም ሊያሳድጉ የሚችሉ የተለያዩ ሁኔታዎችን የማመቻቸትና የአሰራር ስርዓቶችን መዘርጋት የፖሊሲው ማዕቀፍ ትኩረት ሆኖ ይቀጥላል።

### 3.4.1. ግቦች

ሀ. ወላጆች/ አሳዳጊዎች ወቅታዊና ተገቢ የሆነ ፍቅር የተሞላበት ምላሽ-ሰጭ እንክብካቤ ለመስጠት የሚያስችል ግንዛቤና ክህሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፤

ለ. ሕፃናት ከወላጆች/ አሳዳጊዎች ወቅታዊና ተገቢ የሆነ ምላሽ-ሰጭ እንክብካቤ እንዲያገኙ ይደረጋል።

### 3.4.2. ማስፈጸሚያ ስልቶች

ሀ. በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦችን እና ቡድኖችን (የሀይማኖት ድርጅቶች፣ የሴቶች ማህበራት፣ ዕድሮች፣ ማህበረሰቡ እንደ መልካም አርአያ የሚወስዳቸው ግለሰቦችና የመሳሰሉት) በማሳተፍ ማህበረሰብ አቀፍንቅናቄ በመፍጠር ስለ ምላሽ-ሰጭ እንክብካቤ እና ቅድመ ማነቃቂያ አስፈላጊነት ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት፤

ለ. የምላሽ-ሰጭ እንክብካቤ እና ቅድመማነቃቂያ በተለያዩ ስልጠናዎች እና አገልግሎቶች (በሁሉም ደረጃ ባሉ የጤና ባለሙያዎች ስልጠና፤በሴቶች ልማት ሰራዊት፤ በማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ባለሙያዎች/ሰሻል ወርከሮች/የህፃናት ባለሙያዎች) ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል።

እነዚህ ባለሙያዎች የህብረተሰቡን ክህሎት ለማስተማር ብቁ እንዲሆኑ ማድረግ፤

ሐ. በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙና ለጥቃት ተጋላጭ ለሆኑ ሕፃናት ልዩ ትኩረት በማድረግ ምላሽ ሰጪ የሕፃናት እንክብካቤ እና ቅድመ-ማነቃቂያ ተደራሽ የሚሆኑበት ስርዓት ተዘርግቶ መተግበር፤

መ. የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች፣ ነርሶች፣ አዋላጆች፣ ሀኪሞች፣ በጤና ማዕከላት፣ በሕፃናት ማቆያና በቤት ለቤት ጉብኝት አገልግሎት ወቅት ለወላጆች/ አሳዳጊዎች የምክር አገልግሎትና ሰርቶ የማሳያ ፕሮግራም ይተገብራሉ፤

ሠ. በወረዳ፣ በዞን፣ በክልልና በማዕከል የሚገኙ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ጉዳዩ ያገባናል የሚሉ አካላትን በማስተባበር የምላሽ-ሰጭ እንክብካቤና የቅድመ ማነቃቂያ አስፈላጊነትን በተመለከተ ቀጣይነት ያለው ስራ እንዲተገበር ያደርጋሉ ለተግባራዊነቱ ክትትል ይደረጋል፡

ረ. በሆስፒታሎች፣ ጤና ጣቢያዎችና በሕፃናት ማቆያዎች አግባብነት ባላቸው ቁሳቁስ የተደራጁ የሕፃናት መጫወቻ እና የቅድመ ማነቃቂያ ተግባራት የሚከናወኑባቸው ስፍራዎች ይዘጋጃሉ ለነዚህ ስፍራዎችም ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች ይመደባሉ፣ የቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቶ ይተገበራል፡፡

# ክፍል አራት

## 4. ማስፈፀሚያ ማዕቀፎች

### 4.1. ተቋማዊ አቅምን ማጠናከር

የፖሊሲውን ማዕቀፍ ራዕይና ተልዕኮ ለማሳካት በጤና፣ በትምህርት፣ በሴቶችና ህፃናት፣ በማህበራዊ፣ በፍትህ፣ በግብርና ሚኒስቴርና እንዲሁም በሌሎችም ዘርፎች የሚገኙ በየደረጃው ያሉ ተቋማት አግባብነት ያለው የሰው ኃይልን፣ መሠረተ ልማትን፣ ቴክኖሎጂን፣ ፋይናንስንና ሌሎች ግብዓቶችን በማሟላት በቂና አስተማማኝ አቅም እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

### 4.2. የአሰራር ማዕቀፍ

የፖሊሲውን ማዕቀፍ መተግበር የሚያስችሉ ስትራቴጂ፣ የድርጊት መርሀ-ግብር እና እቅዶች ተቀርጸው ተግባር ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ ማዕቀፎቹ ሲዘጋጁ በየደረጃው የሚገኙ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ እርስ በርስ በመናበብና በመቀናጀት የሚዘጋጁና የሚተገበሩ ይሆናሉ፡፡

### 4.3. የፋይናንስ ምንጭ

ሁሉም የቅድመ ልጅነት ዘመን እድገትና ትምህርት ላይ የሚሰሩ ሴክተሮች/ዘርፎች የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ነባራዊ ሁኔታ መሰረት ያደረገ በቂና አስተማማኝ በጀት ከመንግስት፣ ከግልና ከአለምአቀፍ ምንጮች እንዲያገኙ የሚደረግ ሲሆን፣ ከእነዚህ የሚገኙ የፋይናንስ አቅርቦቶች ሴክተር መስሪያቤቶችበተናጠልም ሆነ በተቀናጀ መልኩ በፋይናንስ ህግና ደንብ መሠረት በተጠናከረ ሁኔታ መምራትና ማስተዳደር ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ማህበረሰቡየፋይናንስና የግብዓት ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም በሀብት አጠቃቀምና ውጤታማነት ዙሪያ ክትትል በማድረግ ይሳተፋል፡፡

### 4.4. የክትትልና ግምገማ አሰራር ማጠናከር

የፖሊሲውን ማዕቀፍ ውጤታማነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ጠንካራ የክትትልና ግምገማ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ በየተቋማቱ የሚዘጋጁ ስትራቴጂክ ዕቅዶችም ይህንን ታሳቢ ያደረገ የክትትልና ድጋፍ ማዕቀፍ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ለማጠናከር የሚቋቋሙ የጋራ ፎረሞች (መድረኮች) እና አሰራሮች ወቅታዊ ምላሽ ሰጪ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

የክትትልና ግምገማ ሂደቱን የሚያግዙ አመላካቾች ዓለም አቀፍ መለኪያዎችን ወደ ሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ በመቀየር የሚዘጋጁ ሲሆን የቅድመ ልጅነት ዘመን እድገት፣ መዳበርና ትምህርት አገልግሎቶችን በየጊዜው በመገምገም የሚመለከታቸው ሴክተር መስሪያ ቤቶች ሪፖርት ያደርጋሉ፡፡

የቅልዘእት አገልግሎት አቅርቦትን ጥራት ለማሳደግ ጥራት ያለው ምርምርን የማስተባበር፣ ተሞክሮን የመቀመር እና ግኝቶችን በስፋት የማሰራጫ ዘዴዎች እና የተግባር ሰነዶችይ ቀመጣሉ፡፡

# ክፍል አምስት

## 5. በቅልዘእት አገልግሎት አቅርቦት የባለድርሻ አካላትና አጋሮች ሚናና ኃላፊነት

### 5.1. የባለድርሻ አካላት ተግባራትና ኃላፊነት

የቅልዘእት አመራር፣ አገልግሎትና አቅርቦት በባለድርሻ አካላት አስፈላጊውን ቅንጅት በመፍጠር በጋራ የሚመራ ይሆናል። በዚሁም መሰረት ባለድርሻ አካላት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናሉ።

#### 5.1.1. የትምህርት ሚኒስቴር

ሀ. በቅልዘእት ላይ ስትራቴጂ፣ የመተግበሪያ መመሪያዎችንና ሌሎች ሰነዶችን ያዘጋጃል፤

ለ. ለቅድመ አንደኛ መምህራንና አመቻቾች ስልጠና ይሰጣል፣ የመማሪያ ቁሳቁሶችን ያዘጋጃል፣ እንዲሁም ደረጃዎችንና ጥራትን ያረጋግጣል፤

ሐ.ለቅድመ ልጅነት ዘመን ሥርዓተት ምህርቶች ያዘጋጃል፤ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ የቅድመ አንደኛ መርሀ-ግብሮችን ይቆጣጠራል፤

መ. የቅድመ አንደኛ ትምህርት ማዕከላትና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ቤት ዝግጁነት ፕሮግራሞችን እውቅና ይሰጣል፤

ሠ. ቀዳሚ ማነቃቃትን በተመለከተ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ የወላጆች ትምህርት መማሪያ ማስተማሪያ ያዘጋጃል። ልዩ ፍላጐት ያላቸውን ሕፃናት የመለየት፣ የመዳሰስና የማነቃቃት ሥራ ይሰራል፤

ረ. የአቅም ግንባታና የአህዝቦት ሥራዎችን በመሥራት ግንኙነቶችን በማመቻቸትና ትስስሮችን በማጠናከር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

ሰ. አቅመ ደካማ ህጻናትን እንደ አካል ጉዳተኛ ልጆች በቅድመ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ማካተት የሚቻልበትን መንገዶች በመመርመር ሁሉን አቀፍ የቅድመ መደበኛ ትምህርትን ያስተዋውቃል

#### 5.1.2. የጤና ሚኒስቴር

ሀ. የጤና ሚኒስቴር በቅልዘእት ላይ የዘርፉን ስትራቴጂ፣ የመተግበሪያ መመሪያዎችንና ሌሎች ሰነዶችን ያዘጋጃል፤

ለ. የጤና ባለሙያዎችን በማሠልጠንና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በመስራት የማህበረሰብ ንቅናቄ ያካሂዳል፤

ሐ. በጤናው ዘርፍ ባሉ መዋቅሮች አማካኝነት የጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራምን ጨምሮ ለእናቶች፣ ለጨቅላ ሕፃናት፣ ለህፃናትና ለማህበረሰቡ የጤና አገልግሎትን ለማድረስቁልፍ ሚና ይጫወታል፤

መ. ያልተካተቱ የቅልዘእ አገልግሎቶችን በቤተሰብ ጤና ፓኬጅ ውስጥ ያካትታል። ከሌሎች የቅልዘእት ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል።

ሠ. የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ከማህበረሰብ አቀፍጤና መልዕክተኞች ጋር በመተባበር የቀልዘእት አገልግሎቶችን በቤትና በጤና ኬላዎች እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

ረ. የጤናው ዘርፍ ከፅንሰት እስከ 3+ ዓመት ባለው ወቅት የሚሰጡ የቅልዘእት አገልግሎቶች ላይ የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፡፡

### 5.1.3. የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

ሀ. በቅልዘእት ላይ የሴክተሩን ስትራቴጂ፣ የመተግበሪያ መመሪያዎችንና ሌሎች ሰነዶችን ያዘጋጃል፤

ለ. ዘርፉ በተለያዩ ባህሎች ውስጥ የሚገኙ ጠቃሚ የልጅ አስተዳደግ ዘዴዎችን የመለየት፣ የማዳበርና የማስፋፋት ስራዎችን ያከናውናል፤

ሐ. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በሕፃናት ዕድገት ላይ ስለሚያስከትሉት አሉታዊ ተፅዕኖ በማስተማር ለማስወገድ ይሰራል፤

መ. የሕፃናት መብት፣ ጥበቃና እንክብካቤ እንዲጎለብት ይሠራል። ስለሕፃናት መብትና ደህንነት ግንዛቤ ይፈጥራል፤

ሠ. ጥቃት የደረሰባቸው ሕፃናት ጥበቃ፣ድጋፍ፣ እንክብካቤ እና የተሃድሶ አገለግሎቶችን እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሰራል፤

ረ. በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ሕፃናት የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

ሰ. ሁሉም ሕፃናት የቅልዘእት አገልግሎትን ያለመድልዎ እኩልማግኘታቸውን ያረጋግጣል፣

ሸ. የህፃናት ማቆያዎች በሁሉም ተቋማት እንዲስፋፉ ማድረግና የግል የሕፃናት ማቆያዎችን ቅልዘእትን መሰረት አድርገው መስራታቸውን ይከታተላል፤

ቀ. ለሕፃናት ምቹ የሆኑ የመዝናኛና የመጫወቻ ቦታዎች እንዲመቻቹ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

በ. ማህበረሰብ አቀፍ የቅልዘእት አገልግሎት መስጫ ማእከላት እንዲቋቋሙ ይደረጋል፣

ተ. የሕፃናት፣ የእናቶችና የሴቶች መብቶችን ለማስጠበቅ የማህበረሰብ የንቅናቄ ሥራዎችን ይሰራል፣

ቸ. የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ለመከላከል የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓትን በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፤

ነ. በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን ማህበራዊ የደህንነት ፖሊሲውን መሰረት አድርጎ ችግሮቻቸውን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓቶችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

ኘ. በሥራ ቦታ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የሕጻናት እንክብካቤ ተቋማትን ያስተዋውቃል። ለነፍሰ ጡር እና ለሚያጠቡ እናቶች ተገቢውን እንክብካቤ እና ጥበቃን ለማረጋገጥ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ያስተገብራል።

አ. ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመተባበር ለተለያዩ ችግሮች የተጋለጡ ሕፃናት የተሃድሶ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፣

### 5.1.4. ወላጆችና አሳዳጊዎች

ሀ. ወላጆችና አሳዳጊዎች በሕፃናት ሕይወትውስጥ በጣም ወሳኝ ድርሻ ያላቸው በመሆኑ በልጆቻቸው ዕድገት ላይ ቁልፍ ሚናይጫወታሉ። ሚናቸውም የሕፃናቱን ማህበራዊ ሕይወት ማሳደግ እንዲሁም ለሕፃናት መልካም ባህርይ፣ የሕይወት ክህሎትን መንፈሳዊነትን፣ ባህልንና ሥነ-ምግባርን ማስተማር የመሳሰሉ ናቸው። ለሕፃናት ዕድገት ምቹ የሆነ አካባቢንየመፍጠርና ቀዳሚ ማነቃቃትን የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው።

ለ. የሕፃናቱ መሰረታዊ ፍላጎት መሟላቱን፣ የተመጣጠነ ምግብና የጤና እንክብካቤ ማግኘታቸውን ክትባትና የዕድገት ክትትል የተደረገላቸው መሆኑን መከታተልና ማረጋገጥ አለባቸው።

ሐ.የሕፃናቱ ልደት መመዝገቡን፣ የአካል ጉዳት/ ልዩ ፍላጎት ካሉ በተጨማሪም ልዩ ተሰጥዖ ያላቸውን ሕፃናት ቀደም ብሎ መለየቱንና ድጋፍ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል።

መ. ወላጆች/ አሳዳጊዎች የሕፃናትን መብቶች ማክበርና ማስከበር፣ የትምህርትና የጨዋታ ቁሳቁሶችን ማቅረብና ሕፃናቱን ከቅልዘእት አገልግሎት ጋር በጊዜው መገናኘት አለባቸው።

ሠ. ወላጆች/ አሳዳጊዎች የማህበረሰብ አቀፍ ጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም፣ የማህበረሰብ አቀፍ ቅድመ አንደኛ ትምህርት ማዕከልና መደበኛ ያልሆነ የትምህርት ቤት ዝግጁነት ኘሮግራም አባልናቸው።

## 5.2. የአጋሮች ተግባራትና ኃላፊነት

አጋር አካላት በፖሊሲው ማዕቀፍ የተጠቀሱት የአሰራር ስርዓቶች እንደተጠበቁ ሆነውከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ለመስራት የሚያስችሉ የአሰራር ስልቶችን በመቀየስ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናሉ።

### 5.2.1. ማህበረሰብ

ሀ. ማህበረሰቡ ወላጆች/ አሳዳጊዎች ለልጆቻቸው ሁለንተናዊ የዕድገት ፍላጐቶች መሟላት የሚያደርጉትን ጥረት ይደግፋል። ማህበረሰቡ የቅልዘእት አገልግሎት ለሕፃናት ተደራሽ እንዲሆን፣ ከአደጋ ነፃ አካባቢ እንዲኖርና አስፈላጊ ቁሳቁሶች እንዲቀርቡ ያደርጋል።

ለ. ማህበረሰቡ የሕፃናት መብቶችን ይጠብቃል፣ እንዲሁም የሕፃናትን ሁለንተናዊ ዕድገት ለማፋጠን የሚረዱ ድጋፎችን ለማግኘት ይንቀሳቀሳል።

ሐ. ማህበረሰቡ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሕፃናትን ፍላጐት በቀበሌው/ በአካባቢው/ ያሟላል፣ በቅድመ የልጅነት እድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ሕፃናት አገልግሎት ይሰጣል ከሌሎች አገልግሎት ሰጪዎችም ጋር ይገናኛል ይተባበራል።

መ. የሕፃናት መብት እንዲከበር ጥብቅና ይቆማል። ለሕፃናት እንክብካቤ፣ ጤናና አመጋገብ አማራጭ አቀራረቦችን ያመቻቻል።

### 5.2.2. ገንዘብ ሚኒስቴር

ሀ. የገንዘብ ሚኒስቴር ለቅልዘእት በጀት መመደብና በሁሉም የልማት ዕቅድ ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች የቅልዘእት ኘሮግራም እንዲካተት ያደርጋል፤

ለ. የቅልዘእት ኘሮግራምን ለማገዝና ለሁሉም ተሳታፊ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች አስፈላጊውን ሀብት ለማግኘት አገር በቀልና ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን በማንቀሳቀስ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

ሐ. በሀገራዊና ዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች መካከል አጋርነትን በመፍጠር ረገድ ጠንካራሚና ይጫወታል፤

መ. ባለበጀት መስሪያ ቤቶች የበጀት ጥያቄያቸውን በሚያቀርቡበት ወቅት የቅድመ ልጅነት ጉዳይን በማካተት መበጀታቸውን ይከታተላል።

### 5.2.3. የፍትህ አካላት

ሀ. የፍትህ አካላቱ በሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችንና ብዝበዛዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ የህግ ትምህርቶችን ይሰጣሉ፤

ለ. መብቶችን በማስከበር ረገድ ክፍተት ያለባቸውን ህጎች ያሻሽላሉ፣ ህጎች በተገቢው መንገድ ተግባራዊ እንዲሆኑ ይሰራሉ፤

ሐ. ጥቃት ለደረሰባቸው ሕፃናት ፍትህ እንዲያገኙ ያስችላሉ፤

መ. ምቹ የሕፃናት ችሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋሉ፤

ሠ. ለፖሊስ፣ ለአቃቤ ህግና ለዳኞች የሕፃናት መብቶችን በአግባቡና በላቀ ሁኔታ መተግበር እንዲችሉ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ይሰራሉ፤

ረ. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ጥቃት የደረሰባቸውን ሕፃናት ተገቢውን የተሃድሶ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋሉ። በፍትህ ስርዓት ውስጥ የሚያልፉ ሕፃናትን መረጃ ያደራጃሉ፣ እንዲሰራጩ ያደርጋሉ፤

ሰ. የሕፃናት ልደት ምዝገባን በአግባቡ ተፈፃሚ እንዲሆን የህብረተሰቡን ግንዛቤ ያጎለብታል፣ የአሰራር ስርዓቱን በማዘመን ተደራሽ ያደርጋል።

### 5.2.4. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

ሀ. ይህ ዘርፍ ለቅልዘእት ፕሮግራም አጋዥ የሆኑ አገርበቀል መልካም የወላጅነትና የልጅ አስተዳደግ ባህሎችን ለይቶ በማጎልበት የራሱን ሚና ይጫወታል፤

ለ. የሕፃናት ሙዚቃዎችና ስነ-ጥበባት በስፋት እንዲሰሩና እንዲያድጉ ያደርጋል፤

ሐ. የሕፃናት መፃህፍትንና፣ በአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች የተሰሩ መጫወቻዎችን፣ የልጆች ሙዚቃ እና ስነ-ጥበብን አቅፎ የያዘ የሕፃናት ቤተ-መፃህፍት አገልግሎቶች ያስፋፋል፤

መ. ሆቴሎችና የመዝናኛ ቦታዎች ሕፃናትን ባማከለ መልኩ አገልግሎት መስጠታቸውን ያረጋግጣል።

### 5.2.5. መገናኛ ብዙሀን

ሀ.የቅድመ ልጅነት እድሜ ክልልን መሰረት ያደረገ የልጆች የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥንና የጋዜጣ ፕሮግራም እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

ለ. የቅድመ ልጅነት ዘመን እድገትና ትምህርት ትኩረት የሚሻ ጉዳይ መሆኑን ለህብረተሰቡ ግንዛቤ በማስጨበጥ የቅልዘእት አገልግሎት ተጠቃሚነትን የማጠናከር ስራ ይሰራል፤

ሐ. ሁሉም የቅልዘእት ባለድርሻ አካላት ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ የማነቃቃት ስራ ይሰራል።

### 5.2.6. የግብርና ሚኒስቴር

ሀ. የተለያዩ ፕሮግራሞችን በመቅረፅ የምግብ ዋስትናን ያረጋግጣል፤

ለ. ባለው የስራ መዋቅር መሰረት የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን በመጠቀም ለወላጆች ስለአልሚ ምግቦችና የእንስሳት ተዋፅኦ ለሕፃናት እድገትና መዳበር ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ ሙያዊ ስልጠና፣ ምክርና ድጋፍ ይሰጣል።

### 5.2.7. የውኃ መስኖ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር

ሀ. የንጹህ የመጠጥ እና የንጽህና መጠበቂያ ውኃ አቅርቦት ላይ ይሰራል፤

ለ. ስለ ውኃ አጠቃቀም የማህበረሰቡን ግንዛቤ ያዳብራል፤

ሐ. የኢነርጂ ኃይል አቅርቦትን ያመቻቻል።

### 5.2.8. የሰላም ሚኒስቴር

ሀ. የሕፃናትን ደህንነትና መብት ያስጠብቃል፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ይሰራል፤

ለ. በአስቸጋሪ ሁኔታ የሚገኙ ሕፃናት ልዩ ከለላና ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

ሐ. በሕፃናት ሰላምና ደህንነት ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል።

### 5.2.9. የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር

ሀ. መኖሪያ አካባቢዎችና ህንፃዎች ለሕፃናት ደህንነታቸው የተጠበቀና ምቹ የሆኑ የመጫዎቻ ቦታዎችን ያመቻቻል፤

ለ. የቅድመ አንደኛ ትምህርት ተቋማትን በተመለከተ የግንባታ ፕላን ይሰጣል ጥራቱንም ይቆጣጠራል፤

ሐ. አቅምን መሰረት ያደረጉ የመጫዎቻ ዕቃዎች እንዲቀርቡ የቴክኒክ እገዛ ያደርጋል።

### 5.2.10. የከፍተኛ ትምህርት፣ የስልጠናና የምርምር ተቋማት

ሀ. ለቅልዘእት አገልግሎት አስፈላጊውን የሰው ሀይል በየደረጃው ያሰለጥናሉ፤

ለ. የቅልዘእት ዘርፍን ጥራትና ተደራሽነትን ለማሻሻል ችግር ፈቺ የሆኑ ጥናትና ምርምሮች እንዲሁም የፈጠራ ውጤቶችን በማፍራት የማማከር ስራ ይሰራሉ፤

ሐ. የተወሰኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቅልዘእት የልህቀት ማዕከል ሆነው እንዲወጡ ይመቻቻል።

### 5.2.11. የዕምነት ተቋማት

ሀ.የእምነት ተቋማት ለሕፃናት የቅልዘእት አገልግሎት በመስጠትና በመደገፍ ጠቃሚ ሚና ይጫወታሉ፤

ለ. ልጆች በስነ-ምግባር የታነጹና ግብረ-ገብነት ያላቸው እንዲሆኑ መንፈሳዊ ትምህርት ይሰጣሉ፤

ሐ. በተጨማሪም አቅም የማጎልበት፣ የማስተማር፣ የማስተዋወቅና ሀብት የማፈላለግ ሚና ይኖራቸዋል።

### 5.2.12. የልማት አጋሮች

ሀ. የልማት አጋሮች የገንዘብ፣ የቁሳቁስና የቴክኒክ ድጋፍ በማድረግ ለቅልዘእት አገልግሎት እገዛ ያደርጋሉ፤

ለ. የቅልዘእት አገልግሎትን በማስተዋወቅና የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሻሻል ረገድ የፖሊሲ ማዕቀፉን ተግባራዊነት ያግዛሉ፤

ሐ. አቅምን በመገንባት፣ በአጋሮች መካከል ትስስርን በመፍጠርና በማጠናከር ረገድ ሚናቸውን ይወጣሉ።

### 5.2.13. መንግስታዊ ያልሆኑ ሲቪክ ማህበራት

ሀ. የቅልዘእት አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፤

ለ. ለፖሊሲው ማዕቀፍ ተፈፃሚነት የሀብትና የቁሳቁስና ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋሉ፤

ሐ. በቅልዘእት ዙሪያ የአቅም ማጎልበቻ ስራዎችን ይሰራሉ፤

መ. የቤተሰብን አቅም በማሳደግ ሕፃናት አስፈላጊውን ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያገኙ ይሰራሉ፤

ሠ. የቅልዘእት ፖሊሲ ተፈፃሚ እንዲሆን ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ጥናትና ምርምሮች እንዲሰሩ የበኩላቸውን ድጋፍ ያደርጋሉ።

### 5.2.14. የግል ቅልዘእት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት

ሀ. የግል የቅልዘእት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (ት/ቤቶች፤ የሕፃናት ማቆያዎች፤ የሕፃናት የመዝናኛ፣የስብእና ልማት ማዕከላት ወ.ዘ.ተ...) ደረጃውን መሰረት በማድረግ ቁሳቁሶችን ያሟላሉ፤

ለ. የባለሙያዎችን አቅም በመገንባት ለሕፃናት ተስማሚ አካባቢን በመፍጠር ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት ይሰጣሉ።

### 5.2.15. የግሉ ዘርፍ

ሀ. በየተቋሞቻቸው ውስጥ የሕፃናት ማቆያዎችን በማቋቋም እናቶችና ሕፃናትን መንከባከብ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ያስፋፋሉ፤

ለ. በአካባቢያቸው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ላሉ ሕፃናት ድጋፍ በማድረግ በዘላቂነት የሚያድጉበትን ሁኔታዎች ያመቻቻሉ፤

ሐ. ለፖሊሲው ተግባራዊነት የሚያግዙ የተለያዩ የገንዘብና ቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ይወጣሉ። እንደ አስፈላጊነቱ የቅልዘእት አገልግሎትም ይሰጣሉ።

## መዋቅር አስተዳደር እና ቅንጅት

የቅድመ ልጅነት ፖሊሲ ማዕቀፍ አተገባበርን ማስተባበር የሰስቱ ሴክተሮች (የጤና፣ የትምህርት፣ የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ) ኃላፊነት ሲሆን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶቹ በሚያደርጉት ስምምነት በየሁለትዓመቱ ሰብሳቢ ወይም አስተባባሪ በየተራ በመሰየም የወልና የግል ኃላፊነታቸውን ይወጣሉ። አስተባባሪው ሴክተር/ሚኒስቴር መስሪያ ቤትም ቀጥሎ የተመለከቱትንሀላፊነቶቸ ይወጣል።

ሀ. ስቲሪንግ/መሪ ኮሚቴ ያቋቁማል፣ ኮሚቴውን በሊቀ መንበርነት ወይም በሰብሳቢነት ይመራል፤

ለ. በዓመት ሁለት ጊዜ የሚደረገውን አጠቃላይ ስብሰባ ያዘጋጃል እና ይመራል፤


ሐ. መዛግብቶችንና ቃለጉባኤዎችን በማደራጀት ይይዛል፤

መ.ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች የግንኙነትና የመላላክ ስራዎችን ይሰራል፤

ሠ. የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት ለስቲሪንግ ኮሚቴ ያቀርባል።

ረ. የስቲሪንግ ኮሚቴ አባላትን በመወከል፣ PECDE ፕሮግራም ትግበራ ላይ ለከፍተኛ ደረጃ የፖሊሲ ኮሚቴ/ለሚኒስትሮች ኮሚቴ ወቅታዊ መረጃ ይሰጣል።

*ስዕል 1:* ***የ ቅልዘእት (ECDE) መዋቅር፣ አስተዳደር እና ቅንጅት***




- **ከፍተኛ የፖሊሲ አመራር ኮሚቴ/ የሚኒስትሮች ኮሚቴ:** ይህ ኮሚቴ ከጤና፣ ከትምህርት፣ ከሴቶች እና ከማህበራዊ ጉዳዮች ዘርፍ የተውጣጡ ሚኒስትሮችን/ሚኒስትር ዴኤታዎችን ያቀፈ ነው። ይህ ኮሚቴ በማስረጃ ላይ የተመሰረተ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን የመስጠት ኃላፊነት አለበት።
- **ብሔራዊ የቅልዘእት ፕሮግራም አስተባባሪ ሴክተር /የስቲሪንግ ኮሚቴ አስተባባሪ/:** ከሶስቱ ሴክተሮች አንዱ ማለትም ከጤና፣ ከትምህርት፣ ከሴቶች እና ከማህበራዊ ጉዳዮች በየሁለት ዓመቱ እየተቀያየረ ብሔራዊ የቅልዘእት ፕሮግራም ትግበራን የማስተባበር እና የስቲሪንግ ኮሚቴ ሰብሳቢ የመሆን እንዲሁም የቅልዘእት ፕሮግራም አፈፃፀም ላይ ለሚኒስትሮች ኮሚቴ ወቅታዊ መረጃ የመስጠት ኃላፊነት አለበት።
- **ብሔራዊ ስቲሪንግ ኮሚቴ:** ከመንግስት ሴክተሮች እና መንግስታዊ ያልሆኑ አጋር ድርጅቶች የተውጣጡ በቅልዘእት (ECDE) ላይ የሚሰሩ አባላትን (ስራ አስኪያጆች) የያዘ ነው።
- **ቁልፍ ባለድርሻ አካላት/ የመንግስት ሴክተሮች፡-** በዚህ የፖሊሲ ማዕቀፍ ውስጥ ሚናቸውና ኃላፊነታቸው በግልጽ የተቀመጠ መንግስታዊ ዘርፎች ሲሆኑ የብሔራዊ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ናቸው።
- **መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት አጋሮች:** በቅልዘእት ፕሮግራም ትግበራ ውስጥ የሚሳተፉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ናቸው። ሚናቸውና ኃላፊነታቸው በዚህ የፖሊሲ ማዕቀፍ ውስጥ የተዘረዘረ ሲሆን የብሔራዊ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ናቸው።
- **የክልል ስቲሪንግ ኮሚቴ፡-** በክልል ደረጃ ቁልፍ ሴክተር መስሪያ ቤቶችንና አጋር ድርጅቶችን ያካተተ ኮሚቴ ነው።

2015 ዓ.ም.
አዲስ አበባ